# ራእይ፡ ምዕራፍ አራት ክፍል 1

አሜን። ጌታ ይመስገን። [ቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] ይህ በራሱ-... ። የብዙ ሰዎች አመለካከት ይመስለኛል። እዚያጋ ወጣት እህቴ፡ የመጨረሻው አዝማች፡ እጅግ ግሩም ነበር። ስለ እውነት በጣም ወድጄዋለሁ። እንግዲህ ሁላችንም... በአዲስ ዓመት ምሽት መግቢያችን ከዚህ የተሻለ መዘመር የምንችል አይመስለኝም፡ ለዚህ ምሽት ከዚህ በላይ አይኖርም።

2 ዓመቱን በጥሩ ሁኔታ የጀመርነው ይመስላል፥ ኧሃ-ሃህ፡ በዚህ ዓመት ውጪው የተለመደ የኢንዲያና የአየር ሁኔታ ሆኗል፡ ደስ ይላል በረዷማና የሚያንሸራት ሆኗል። ከጆርጂያ እና ከኦሃዮ የመጣችሁ ሰዎች፡ እዚህ አይቻለሁ። እንግዲህ፡ ወንድም ዳውች፡ አንቺም እህት ዳውች ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ በኦሃዮም ተመሳሳይ ነውና። አንድ ቀን... ግን፡ እነዚህ ነገሮች ወደሌሉባት ምድር እንገባለን። ኧሃ-ሃህ። ዋናው ነገሩ ያ ነው።

3 ይህ የአዲስ ዓመት ምሽት፡ ዋዜማ ነው። እና፡ በእርግጥ፡ ሁሉም ሰው ስእለት ይጽፋል ለአዲሱ ዓመት ቃል ኪዳን ትገባላችሁ፡ ከዚያ ከነገ ወዲያ ሁሉም ይከፈታሉ። ከዚያም፡ ያው፡ በየአመቱ አዲስ ገጽ ትገልጣላችሁ፡ በነጋታው ማለዳ ግን ትመለሱበታላችሁ፡ እንደገና ታደርጉታላችሁ።

4 አንድ ልናገር የም—የምፈልገው ነገር ግን አለ ይኸውም፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው ነው፡ "ከዚህ በፊት ያደረግኳቸው ነገሮች እና ስህተቶቼን በሙሉ፡ የኋላየን ነገሮች ሁሉ እየረሳሁ፡ በክርስቶስ ወዳለው የታላቁ ጥሪ ምልክት ለመድረስ እዘረጋለሁ።" የሚጸጽተኝ ብቸኛው ነገር ባለፈው አመት እና፡ ባለፈው ህይወቴ ያደረግኳቸው ስህተቶቼ ብቻ ናቸው፡ ስለዚህ የታላቁ ጥሪ ምልክት ላይ ለመድረስ ግን ጸጋን ብቻ በትህትና እጠይቀዋለሁ። ይህ ነገር የሁላችንም—ምስክርነት እንደሆነ አምናለሁ፡ ሁላችንም እንደዚያ ይሰማናል።

5 በጣም መጥፎ ምሽት ስለነበረ እናዝናለን—ሰዎች መምጣት አልቻሉም። ወንድም ኔቪልን ደወልኩለት፡ መምጣት ይችል እንደሆነ እንኳን አላውቅኩም ነበር። ከዚያም ወንድም ሰካግስ መጣ፡ እርሱም የመጣው ሶስት ፊት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነችው ከኬንታኪ በታች ነው። እ... ወይም፡ "**ይሄን** ያህል ነው፡" እና፡ አንድ ገበሬ ሁለት ጊዜ ጎትቶ አወጣኝ አለ በትራክተር ወደ ኮረብታው ራስ ይዞት ወጣ። እኔም "እንግዲህ፡ ሁለት ወይም ሶስት ኢንች ብቻ ከሆነ እንኳ፡ ከዚያ በላይ አይሁን እንጂ፡ ችግር የለውም፡ ኧሃ-ሃህ፡" በማለት አሰብኩ። መንገዶቹ ግን የሚያስተላልፉ ስለሆኑ ሰዎች እየወጡ እየገቡ ናቸው።

6 አሁን፡ በእርግጥ ዛሬ ምሽት ከተለያዩ አገልጋዮች፡ ከመጡት የተለያዩ አገልጋዮች፡ የምንሰማበት ምሽት ነው። እና ምናልባት ዛሬ ምሽት፡ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ተባብረው የሚመጡ ይሆናሉ። ከዚያ በኋላ አዲሱ አመት ሲደርስ... ሲገባ፡ ያረጀውም ሲወጣ... ለማየት ተቀምጠው ይጠባበቃሉ ብዬ አስባለሁ። አብዛኛውን ጊዜ የመሠዊያ ጥሪ ይደረጋል ይጸለያል—ከዚያም ስእለታቸውንም ለእግዚአብሔር ያደርጋሉ—ስእለቶቻቸውንም ያድሳሉ።

7 ወንድም ኔቪልን ነግሬዋለሁ... እየመጣ እንደሆነ ለማየት ደውዬለት ነበር። አንተ ካልመጣህ፡ የምችለውን ሁሉ ለማድረግ እሞክራለሁ አልኩት። ስለዚህ እስከ ጠዋት እዚህ መድረስ ካልቻለ፡ እንግዲህ፡ እሱ ባለመኖሩ—እኔ ራሴ የምችለውን ያህል አደርጋለሁ። ምናልባት የአስራ-አምስት ደቂቃ፡ ወይም የሆነ ነገር መልዕክት እንዳለኝ በማሰብ፡ ዛሬ ማታ እሞክራለሁ አልኩት። እና፡ በርካታ ሌሎች አገልጋዮች እዚህ ተቀምጠው ሲጠብቁ፡ እያየን ነው።

8 ስለዚህ... በዚህ በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ጀምሬ እንደምቀጥል አስቤአለሁ፡ እንዲሁ ወደፊት እንቀጥላለን፡ አሁን 4ኛው ምዕራፍ እናንሣና፡ እንጀምራለን። እና በዚህ ጊዜ ይሄን ካልጨረስነው፡ በሚቀጥለው ጊዜ እንቀጥለዋለን። ከዚያም በቻልነው ያህል፡ ወደ 5ኛ፡ እና 6ኛ እንቀጥላለን። ይሄን ለማድረግ ጌታ ይርዳን።

9 ከመጀመራችን በፊት፡ ይህን መናገር እፈልጋለሁ፡ ይህም... ከ—ከጥቂት ሰዓታት በፊት አንድ እንግዳ መጥቶብን ነበር... ወንድም ድሩሞንድ ቶም እና ሚስቱ ናቸው። ዛሬ ማታ እዚህ የተቀመጡት እናትና አባቷ ናቸው። እናም ታላቅ የነፍስ-አድን አገልግሎቶችን እና መለኮታዊ የፈውስ አገልግሎቶችን ሲያደርጉ ቆይተው እነሆ ከአፍሪካ ተመልሰዋል። ይህች ጨዋ ሴት፡ የእያትዋ ፈለግ የተከተለች፡ ይመስለኛል፡ በቀደም ለታ፡ የወሳኒ ቤት አገልግሎት ነበራቸው፡ እና ኃጢአተኞች፡ እና ሌሎች ወደ ጌታ መጥተዋል። እግዚአብሔር እነዚያን ወጣት ባልና ሚስት እንዴት እንደሚጠቀምባቸው ያስደንቃል። አንዳንድ የወንጌል አገልግሎት ለመስራት አሁን እዚህ አሜሪካ ውስጥ ናቸው።

10 ምናልባት ከእናንተ ከፓስተሮች... ብጽፈው ይሻለኛል ወንድም ድሩሞንድ... ድራሞንድ፡ አዎን፡ ይህ ስም፡ ሁሌ ይምታታብኛል። ለምን ጥሩ የእንግሊዝኛ ስም ቀይሮ ይህን አይተወውም? እስቲ ቁጥር እንስጠው፡ ምን ትላላችሁ፡ ምክንያቱ እኔ አልችለውም፡ በጭራሽ። ግማሾቻችን እንችለዋለው ብዬ አላስብም። ትክክለኛው አጠራር፡ “ድራሞንት፡” እና እህት ሻርሎት፡ ይመስለኛል፡ ከእናንተ ሊጋብዛቸው የሚፈልግ ሰው ካለ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያናችሁ መግባታቸውን መስማት እፈልጋለሁ።

11 ይህች እመቤት፡ እህት ሻርሎት፡ ገና ህጻን ልጅ ናት። ቀደም ሲል እዚያ ማዶ በአፍሪካ የገጠማቸው አጋጣሚዎች ሁሉ፡ ለሚዳ፡ እያጫወተቻት ነበር፡ እና እላችኋለሁ... ቢሊ፡ የድሮ ዘመን የሚመልሱ ናቸው፡ አፍሪካውያን እንደሚናገሩ ይመስል ነበር። ስለዚህም ሰልፉ እዚህ እንዳለ ሁሉ በዚያም ደግሞ ያው ነው።

12 ወንድም ድሩመንድን እ... እና እህት ሻርሎት፡ በቤተ ክርስያኖቻችሁ ካምፔን ለማድረግ መጥራት ለምትፈልጉ ሁሉ፡ ካሰባችሁበት፡ በMElrose 7-3945 ወንድም ቶኒ ዛብል ብላችሁ ደውሉ። አንዳንዶቻችሁ አገልጋዮች፡ መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ ወንድማችንን እንድትቀበሉት እመክራለሁ... ጥሩ ሰባኪ ነውና፡ ቅን ልጅ፡ ገና እየጀመረ ያለ፡ በእውነት ጅማሬ የሚያስፈልገው ነው። በጭራሽ የማይፈራ፡ መልካም ልጅ ነው፡ እጅግ እወደዋለሁ። እንግዲህ፡ አስታውሱ፡ MElrose 7-3945 ነው። ምናልባት ካስፈለጋችሁ ብዬ፡ ይህች ትንሽ ካርድ እዚህ አስቀምጥላችኋለሁ... ካርዳቸው ነው፡ ቁጥሩን መጻፍ ካልቻላችሁ፡ ምናልባትም፡ መጥታችሁ መውሰድ ትችላላችሁ፡ ወይም ከዛሬ ምሽት ልዩ ልዩ መርኃ ግብሮች በኋላ። ቁጥራቸውን ውሰዱና በአብያተ ክርስትያኖቻችሁ

ጉባኤ ውስጥ መጋበዝ ከፈለጋችሁ ደውሉላቸው፡ ወይም እነርሱን ሊጠራቸው የሚችል የምታውቁት ሰው ካለ፡ ምክንያቱ አሜሪካ ዙርያ ክሩሴድ ላይ ናቸውና።

13 አፍሪካ ወደ አሜሪካ ሚሽነሪዎችን መላክ መቻልዋ! አይደንቅም ወይ? የሚፈለጉበት ቦታ፡ እዚሁ ጋር ነው፡ ከዚያ ይልቅ እጅግ የከፋ ነውና።

14 እሺ ጌታ ለሌላ ዓመት ስለጠበቃችሁ ስንቶች ደስታ እና ሐሴት ይሰማችኋል? እነሆ አሁን ደግሞ፡ ወደ መንገዱ ፍጻሜ ተቃርበናል። እግዚአብሔርም ኃጢአታችንንና ድክመቶቻችንን ሁሉ ይቅር እንዲለን እንጸልያለን።

15 አሁንም፡ ከመጀመሬ በፊት ይህን ማለት እፈልጋለሁ። ለእያንዳንዳችሁ መልካም ምኞቴ፡ በጣም የተሳካ፡ እና የተባረከ እና ጤናማ አዲስ አመት እንዲሆንላችሁ፡ እመኛለሁ። እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር ይሁን! በአካላዊ፡ በመንፈሳዊ፡ እና በገንዘብ፡ እና በንብረት እደጉ። እግዚአብሔር በእናንተ ላይ የሚያመጣውን ሁሉ፡ እንዲያደርገው እጸልያለሁ።

16 እኔ ራሴ፡ ከፊቴ አዲስ አመት እየተደቀነብኝ ነውና፡ ከፊቴ ያለውን እግዚአብሔር ብቻ ያውቀዋል። እና ውሳኔዎቻችን ወዲያውኑ መደረግ አለባቸው። ሁሉንም እቃዎቻችንን አዘጋጅተናል። ወንድም ጂም፡ ከመላው ዓለም የተላኩልንን፡ የተለያዩ ጥሪዎች እና ግብዣዎች፡ በዓለም-አቀፍ ደረጃ፡ ወዴት መሄድ እንደሚገባን ለመገንዘብ ቦታ ቦታ አስይዞታል። በስህተት እንዳልመራ እግዚአብሔር ይረዳኝ ዘንድ በፍጹም ልባችሁ እንድትጸልዩ፡ በእውነት የእናንተን ጸሎት እጠይቃለሁ። እ—እኔ... ከምንም በላይ፡ በስሕተት የማይመራ እና ቅን መሆን እፈልጋለሁ። እንግዲህ፡ ጥሩ አመት አሳልፌያለሁ።

17 ብዙ ጊዜ፡ ሰዎች ይሰታሉ። እና እንዲህ ይሉኛል፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እ—እ... እንደ ድሮህ ሌሎች አገልጋዮች እንደሚያደርጉት፡ ወደነዚህ ቦታዎች ሄደህ፡ እነዚህን ነገሮች ሁሉ አታደርግም ወይ... ” ከመጽሐፍ ቅዱሳችን እና ከጌታችን ትምህርት የተማርኩት፡ አ—አንድ ነገር አለ፡ ይህም ኢየሱስ የታይታ ሰው አልነበረም። ያንን እ—አስቀርቷል፡ ልታይ ባይነት አልነበረውም። እያችሁ፡ በጭራሽ፡ የታይታ ሰው አ—አልነበረም። ደቀ መዛሙርቱም እዩኝ ባዮች ናቸው ብዬ አላምንም። ራሳቸውን አሳይተው አያውቁምና።

18 ዛሬ ጀልባዋ ጋር በጣም የተተላለፍንበት ቦታ ይህ ይመስለኛል፡ (ምናልባት የራሴ ሀሳብ ሊሆን ይችላል።) ማለት፡ ስለሁሉም ነገር ጉሰማዎች የምናደርገው፡ ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ እንደማስበው ከቅድስናው ይልቅ ለመታየት ይመስለኛል።

19 በጌታ መምጣት ጊዜ፡ እርሱን በእውነት የተቀበሉትን አስተውላችኋል? ስምዖን ነበር፡ ስለሱ ምንም ተሰምቶ የማይታወቅ ሰው ሲሆን፡ የጌታን መምጣት ይጠባበቅ ነበር። በቤተ መቅደስ የነበረች፡ አይነ ሰውሯ ሃና። በምድረበዳ የነበረው፡ መጥምቁ ዮሐንስ። እንዚህ ናቸው...

20 ዮሐንስ በዘጠኝ ዓመቱ ወደ ምድረ በዳ ሄደ፡ እስከ ሠላሳ ዓመቱ ድረስ ዳግመኛ አልታየም፡ በምድረ በዳው ቆየ። እንደነዚህ ያሉት ሰዎችም በሰውር ያመኑ፡ ትሑታንም፡ የጌታን መምጣት ይጠባበቁ ነበር። ስለ ስብሰባዎቻቸውን ጥሩምባ አልነፉም በታላላቅ ምልክቶችም አልሰቀሉትም (“ጊዜው! ዘመኑ!”) በማለት—እና የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች እና ሌሎች አላደረጉም። እንደዚያ

ሊያደርጉት ለሚፈልጉ ምንም አይደለም፡ ለእኔ ግን፡ ነገሩ፡ የክርስቶስ-ምሳሌ አይመስለኝም።

21 አንድ ጊዜ የገዛ ወንድሞቹ፡ እንዲህ እንዳሉት አውቃለሁ፡ “እነዚህን ተአምራት እና ነገሮች ታደርጋለህ፡ ለምን ወደ—ወደ እየሩሳሌም አትወጣም? እኛም ወደ ፋሲካው በዓል እንወጣለንና፡ ሊቀ ካህናቱን ቀያፋን፡ እና እነዚያን ሁሉ ጠርተን፡ እንዲያውቁ እናድርጋቸው። ሥራህን እንዲያዩ፡ በፊታቸው እንዲሁ አድርግ። አሁንስ፡ ተመልከት፡ ከዓሣ አጥማጆች ጋር ለምን ትዋኛለህ፡ ወንዝ ዳር ላይ፡ ከዝቅተኛ ማሕበረሰብ ጋር፡ ወዘተረፈ? ምነው... ተነስተህ አለም እንዲያየው ለምን አታደርግም? ” አያችሁ?

22 ኢየሱስም፡ “ጊዜአችሁ ሁልጊዜ ነው፡ የእኔ ግን ገና ሰዓቴ አልደረሰም።” ኧሃ-እህ። አያችሁ?

23 ዮሐንስ አንድ ጊዜ... መጥምቁ ዮሐንስ፡ ስለሱ መምጣት በ—በቅዱሳት መጻሕፍት ተነገሮለታል። እንዲህም አለ፡ “ያ፡ ሲመጣም... ” ይኸውላችሁ፡ ከመወለዱ ከሰባት መቶ አሥራ ሁለት ዓመታት በፊት፡ ኢሳይያስ እንዲህ አለ፡ “እነሆ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ይመጣል።” እንዲህ አለ፡ “ተራሮች ሁሉ እንደ ጠቦቶች ዘለሉ፡ ቅጠሎች እጆቻቸውን አጨበጨቡ፡ ኮረብቶች ዝቅ አሉ፡ ሸለቆዎች ከፍ ከፍ ተደረጉ።”

24 እንደዚህ ያሉ ትንቢቶች! በተነገሩ ጊዜ የዛን ዘመን አገልጋዮች... ያን ነገር በሰሙ ጊዜ፡ ምን ያሉ ይመስሏችኋል፡ “አቤት! ያ ታላቅ ነቢይ ሲመጣ፡ ሰዎች ሁሉ የሚያውቀው ይሆናል። እግዚአብሔር የሰማይን ጣራዎች ይዘረጋል፡ የሰማይም ኮሪደሮች ዝቅ ያደርጋቸዋልና፡ የእሳት ሰረገሎች ይወርዳሉ፡ የመላእክት ጭፍራ ወደ ምድር ያጅቡታል።”

25 እርሱ በመጣ ጊዜ ግን፡ መልከ-ጥፉ የተጎሳቆለ በሰውነቱ ላይ የበግ ቆዳ የለበሰ፡ የቆዳ ቀበቶ የታጠቀ ሰባኪ ሆኖ መጣ። ምናልባት በየሶስት ወይም አራት ወሩ ካልሆነ፡ ገላውን የማይታጠብ ይመስላል። በዚያ፡ በምድረ በዳ፡ እስከ ጉልበቱ ድረስ፡ ጭቃ ውስጥ ቆሞ፡ እንዲህ እየሰበከ መጣ፡ “መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና፡ ንስሐ ግቡ!” ወደ ከተሞች ሄዶ አያውቅም። ሊሰማው የሚፈልግ ቢኖር፡ እርሱን የሚሹትን፡ እርሱን ለመስማት ወደ ዮርዳኖስ ይመጡ ነበር። ምን አደረገ? አገሪቱን አንቀጠቀጣት፡ አለምን አንቀጠቀጠ።

26 አሁንም እሱን በማያውቁት ሰዎች ዘንድ ንቅናቄ እየቀጠለ ይገኛል። ኢየሱስ ሲመጣ፡ ራሱን ከታላላቅ ሰዎች ተርታ ፈጽሞ አላሰለፈም። የእርሱ ወደሆኑት መጣ፡ እርሱን ይጠባበቁት ወደነበሩት መጣ። ንቅናቄ የሚሆንላቸውም እነዚያን ነው። ዛሬ የሚያደርገውም ይህንኑ ነው። እግዚአብሔር ወደ ጠራቸው ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ይመጣልና። በተመረጡት መካከል ታላቅ ንቅናቄ አለ። ታላቅ፡ ኃይለኛ ነገር እየተካሄደ ነው፡ ዓለም ግን ስለዚህ ምንም ነገር አያውቅም።

27 እንዲህ መሰላቸው እንጂ፡ አበባ የመሳሰሉ ነገሮች፡ አለም-አቀፍ ሰርጭቶች፡ እና ቴሌቪዥኖች፡ እና የሚሊዮን-ዶላር ሕንፃዎች፡ እና ሁሉም ነገሮች፡ እጅግ ታላላቅ ነገሮች ይሆናሉ ብለው አሰቡ። ይህ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነው። እግዚአብሔር ትልልቅ ነገርን አይመለከትም። ሰው “ሞኝ” የሚለው ነገሮች፡ እግዚአብሔር “ታላቅ” ይለዋል፡ ሰው “ታላቅ” የሚለው ነገር፡ እግዚአብሔር “ሞኝ” ይለዋል። “በስብከት ሞኝነት፡ የጠፉትን፡ ለማዳን ወደደ።”

28 አሁን፡ ስለ ዮሐንስ። ምን ያሉት ይመስላችኋል? “ይኸውላችሁ ይህ ወግ አጥባቂ፡ መልከ-ጥፉ-ፊት ሰው፡ የበግ ቆዳ ለብሶ ከምድረ በዳ የወጣ ሰው። እና፡ በባዶ እግሩ፡ በጭቃ መኃል፡ እየተመላለሰ፡ በዮርዳኖስ ዳርቻዎች፡ ለምን ይቆማል። እንደዚህ ያለ ነገርስ ማን ሰምቶ ያውቃል? ”

29 ኢየሱስም ሲመጣ። “በከብቶች በረት፡ በገለባ ክምር ላይ፡ እና—ከብቶች በዙርያው እምቧ እያሉበት፡ መሲሕ ሆኖ ተወለደ? እ—እና ደግሞ ከእናቱ... እንደ አባቱም፡ በሕገ ወጥ የተወለደ... እናቱ ገና ከመጋባታቸው በፊት እናት ልትሆን ተቃርባለች፡ ለምን፡ ከሕጋዊ ጋብቻ ውጭ የተወለደ ነው። ያ ሰው? ኦህ፡ ማይ! አያችሁ? እነርሱ አላወቁትም እንጂ፡ እርሱ ታላቅ ነበረ። አያችሁ? አላወቁትም።

30 ዛሬም ወንጌልም እንዲሁ “ታላቅ” ነው። ወንጌሉም ከዚህ በፊት ሆኖ በማያውቅ መልኩ እየተናወጠ ይገኛል፡ የሚናወጠው ግን በቅሬታዎች ዘንድ ነው። ልክ ነው፡ እያዘጋጃቸው ይገኛል።

31 “ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ፡ የገዛ ወገኖቹ አልተቀበሉትም።” ለደቀ መዛሙርቱም፡ “በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፡ ይልቁንም ወደ ጠፉት የእስራኤል በጎች ሂዱ እንጂ። ስትሄዱም፡ እናንተን የሚቀበል፡ እኔን ይቀበላል። ወደ አንዲት ከተማ ስትገቡ፡ ካልተቀበሏችሁ፡ የእግራችሁን ትቢያ አራግፋችሁ ውጡ። እናም እውነት እላችኋለሁ፡ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ እነሆ ለሶዶም እና ለጎሞራ ይቀልላችኋል።” እናም እነዚያን ሰዎች አንቀበልም ያሉት ከተሞች ሁሉ እነሆ ዛሬ አመድ ውስጥ ወድቀዋል። የተቀበሏቸው ሁሉ ግን፡ አሁንም ድረስ እንደ ካቴድራል ቆመዋል። በትክክል፡ አያችሁ። መልስ ለመስጠት ረጅም ጊዜ ይወስዳል፤ ግን እግዚአብሔር መልስ ይሰጥበታልና፡ አትጨነቁ። ገና አልጀመርኩም፡ ወደ ራእይ ፈጽሜ አልገባም። አቤት!

> እነሆ፡ ፊቱን አይቼ፡ ላየው እናፍቃለሁ፡
> ስለ ማዳን ጸጋው ለዘለአለም እዘምርለታለሁ፤
> በክብር ጎዳናዎች ላይ ድምፄን ከፍ አድርጌ፡
> ጭንቀት ሁሉ አልፎ፡ ለዘለአለም ደስታ፡ ቤቴ በገባሁ ጊዜ።

32 ደስ ይላል። እስኪ ለፍታ ያህል ራሶቻችን ዝቅ እናደርጋለን። ከዛ በፊት ግን ፍቃደኞች ከሆናችሁ በእግራችሁ ትቆማላችሁን? ይ—ይመስለኛል... መጽሀፍ ቅዱስ “ለጸሎት፡ስትቆሙ፡ ይቅር በሉ፡” ይለናል። የጸሎት ጥያቄ ያላችሁ በተነሳ እጅ እንዲታወቅላችሁ የምትፈልጉት ስንቶች አላችሁ? እግዚአብሔር፡ እንደሚያይ አስታውሱ፡ ሁሉንም ያውቃልና።

33 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ በጌታ በኢየሱስ ስም ወደ መለኮታዊ ቅድስናህ እንቀርባለን፡ ይህ ስም በሰዎች መካከል ከተሠጠው ስም ሁሉ ይልቅ ይበልጣል፡ በሰማይና በምድር ያሉ ቤተሰቦች ሁሉ የተሰየሙበት ስም “ኢየሱስ” ነው።

34 አሁንም ጌታ ሆይ፡ ምስጋናችንን እንድትቀበል፡ እንጸልያለን። በዚህ ተሸኘ ዓመት፡ መጀመሪያ፡ ስንጀምር... በአገልግሎት ስንጀምረው፡ በምስጋና ስንገባበት፡ ቃልህን እያጠናን የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ምን ማለት እንደሆን በመረዳት እንጀምረዋለን። ለማመስገን ስንት ነገር በወረቀት

ላይ ማሰፈር እንችላለን! በዚህ አመት ያገኘናቸው፡ ጠባባብ ማምለጫዎች፡ ሰይጣን ህይወታችንን ሊያጠፋ የሚችልባቸው ነበሩ፡ አንተ ግን አሁንም ከእኛ ጋር አልጨረሰክም። ስለዚህ እነሆ አሁንም እንቀጥላለን። ጌታ ሆይ፡ በዚህ ዓለም ውስጥ የተወለድነው እና ያደግነው አንተን ከፍ ከፍ ለማድረግ እና ለማክበር እንደሆነ እናምናለን።

35 አባት ሆይ፡ ስለ በደላችን እና በጉዞ ሂደት ያደረግናቸው፡ እያንዳንዱ ስሕተታችን በሙሉ ይቅር እንድትለን ዘንድ እንጸልያለን። ዛሬ ማታ ስህተቶቻችንን ሰንናዘዝ፡ ዳግመኛ ቆፍረን እንዳናወጣቸው፡ እነሆ በመርሳት ባህር ውስጥ፡ በጌታ በኢየሱስ ስም ቀብረን፤ ወደዚህ ምልክት፡ ወደ ፍጹም ሰው፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ማደግ ይሁንልን። ዛሬ ማታ አድርግልን፡ አባት ሆይ።

36 ባርያዎችህ ሁሉ ሲናገሩ፡ እያንዳንዳቸው፡ በሕይወት መንፈስ ቅባቸው፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ ዛሬ ይሰበኩ፡ ዛሬ ማታ መልእክቶቹን ወደ ቤተ ክርስቲያን ያምጡ።

37 ጌታ ሆይ፡ በዚህች ትንሽ ጣሪያ ስር ተሰብሰበናልና፡ ለዚህም እናመሰግናለን። የሚያስፈልገን እርሱ ነውና፡ ከሚነድ ሞቅ ያለ እሳት አጠገብ መሆናችን፡ ከራሳችን በላይ ጣራ መኖሩ እናመሰግናለን።

38 ሃብቶቻችን በዚህ ዓለም ውስጥ አይደሉምና፡ በሚመጣው ዓለም ውስጥ ናቸውና። እግዚአብሔር ሆይ፡ ሃብቶቻችን የዘለአለም ህይወት ናቸውና ሌቦች ገብተው በማይዘርፉበት፡ ብልም እንደማይበላው በምንተማመንበት ስፍራ፡ እነሆ ተቀምጠናል። እናም አባት ሆይ፡ በህይወት ዘመናችን ሁሉ፡ ያንን እንድንንከባከብ እንድትፈቅድልን እንጸልያለን።

39 ብቁ አገልጋዮች አድርገን። ጌታ ሆይ፡ ያለፈ ክፉ ሁሉ፡ ከኛ አሰወግድ። አሰወግድልን... የክፋት ሰር እና ምሬት ሁሉ ከሕይወታችን ይወገድ፡ ይህም በፊትህ ትሑታን እና ደጎች እንሆን ዘንድ ነው። አድርግልን፡ ጌታ ሆይ። መጪው ዓመት፡ ካሳለፍናቸው አመታት ሁሉ ይልቅ ያማረ ይሁን። አድርግልን። ከመልእክቶችህ ሰንጠባበቅ ሳለን፡ አቤቱ ከቃልህ፡ ዛሬ ስጠን። በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን። አረፍ አረፍ በሉ።

40 እንግዲህ፡ ያንን ሰዓት እዚያ እንዲህ ሆኖ እያየሁ፡ ወንድሞቼ እንዲጠብቁ ማድረግ ይከብደኛልና፡ ስለዚህ በተቻለኝ ፍጥነት ለመቸኮል እና ይህን ክፍል ለመጨረስ እሞክራለሁ። እና፡ ምናልባት፡ ካልጨረሰን፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ምናልባት ነገ ጠዋት ለመቀጠል እንሞክራለን። እንዲሁም ወንድም ኔቪል ካልደረሰ፡ ወይም ሌላ ነገር ቢሆን፡ እንግዲህ፡ እንደ ጌታ ፈቃድ፡ የሰንደይ ስኩል አገልግሎቱን እኔ ለመሸፈን፡ እሞክራለሁ።

41 እንግዲህ፡ አሁን አትርሱ፤

> እንጸልይ፡ እንጸልይ፡ ብቸኛው መንገድ ነው
> ... ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ለመድረስ፤
> እንጸልይ፡ እንጸልይ፡ የእምነት ጸሎት
> የእግዚአብሔርን በረከቶች ያወርዳሉ።

42 ማሳካት የምትችሉበት መንገድ ያ ብቻ ነው። አብረን እንዘምር። በዚህ አዲስ አመት፡ በቂ ጊዜ አለን።

እንጸልይ፡ እንጸልይ፡ ብቸኛው መንገድ ነው
ከፍ ወዳለ ቦታ ለመድረስ፤
እንጸልይ፡ እንጸልይ፡ የእምነት ጸሎት
የእግዚአብሔርን በረከቶች ያወርዳሉ።

43 ስለዚህ የእምነት ጸሎት የእግዚአብሔርን በረከቶች ካመጣ፡ መጸለያችንን እንቀጥል። ዛሬ ማታ፡ ባለፈው አመት በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ያልነበሩ አዳዲስ ፊቶችን አይተናልና፡ ሐሴት እናደርጋለን። እና እንደኔ፡ ሌሎች ብዙዎች እንዲመጡ ጸሎታችሁን ቀጥሉ። በሌላኛው በኩል ያለውን ግማሹ ምን እንደሚመስል ገና አልተነገረም።

44 አሁን፡ ራዕይ 4ኛው ምዕራፍ 4 እንከፍታለን። መጽሐፍ ቅዱስ የሚፈልግ ሰው ካለ? ምናልባት እኛን መከታተል ከፈለጋችሁ። በጣም ጥሩ፡ ከአስተናጋጆች አንዱ ይምጣና፡ እዚህ ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ክምር አለን። ከባለአደራዎች፡ አስተናጋጆች፡ ወይም አንዳችሁ፡ ቶሎ ብላችሁ ወደዚህ ኑ። ወንድም ዛቤል፤ እና ሌላ አንድ ሰው፡ ኑ። በሁለቱም ጎን ውሰዱላቸውና፡ በመተላለፍያዎቹ እለፉ። ከእኛ ጋር አብሮ መከታተል የሚፈልግ፡ ማንም ቢኖር፡ እንዴ፡ ውሰዱላቸውና ለሚፈልግ ለማንም ሰው ስጧቸው።

አሁንም ከራእይ፡ 4ኛው ምዕራፍ እንድትከፍቱ እንፈልጋችኋለን።

45 እና፡ ደግሞም፡ ከኋላ የተቀመጣችሁ ወደዚህ ወደፊት መቅረብ ከፈለጋችሁ፡ ዛሬ በቂ ቦታዎች አዘጋጅተንላችኋልና ወደዚህ መቅረብ ትችላላችሁ። ራሳችሁን ምቹት እንዲሰማችሁ አድርጉና፡ በቀጥታ ወደ ትምህርታችን እንለፍ እንዳነበው እገዙኝ፡ እና አብረን ሆነን እናጥናው። እዚህ ጋር ወንበሮች አሉ። ባልና ሚስት ሲመጡ አያለሁ። እና ሁለት ወንበሮች እዚህ ጋር አሉ። እዚያ ጋር ላለው ብቸኛውም እዚህ ጋር አለለት። እዚያ ከኋላ ያላችሁ፡ እዚህ ጋር ወንበሮች አሉ። እነዚህ የንፋስ መቅዘፊያዎች ሁለንተናዊ ናቸው ብዬ አስቤ ነበር።

46 እስኪ አሁን፡ ስለ **ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት**፡ በነበሩን የሰምንት-ቀናት ትምህርቶች ስንቶች ተባርካችኋል? አመሰግናለሁ። ጥሩ ስሜት እንዲሰማኝ ያደርገኛል፡ እኔ ራሴ ታላቅ በረከት አግኝቼበታለሁና።

47 አሁን፡ ዛሬ ማታም ወደ 4ኛው ምዕራፍ፡ አሁን እንሄዳለን፡ ዮሐንስ ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ተናግሯል። እና፡ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ከሌሎቹ ሁሉ እጅግ የተመሰቃቀለ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነበር።

48 እና በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የመጨረሻ ክፍል ላይ በጣም አሳዛኝ ነገር አይተናል፡ ኢየሱስ ከተጣለበት ቤተ ክርስቲያን ውጭ ቆሞ፡ መልሶ ለመግባት እየሞከረ፡ ሲያንኳኳ አይተነዋልና። ይህስ ኃጢአት አይደለምን? እስከ ዛሬ ካነበብኳቸው ቅዱሳን ቃላት ሁሉ በጣም አሳዛኝ ይህ ይመስለኛል። ኢየሱስ፡ ቤተክርስቲያኑ አስወጥታው፡ በገዛ በሩ ውጪ ሆኖ፡ ሊያድናቸው ፈልጎ ወደ ውስጥ ሊገባ ሲፈልግ ይታያል። "ለሚከፍትልኝ ማንኛውም ሰው፡ ወደ ቤቱ እንድመለስ ለሚፈቅድልኝ፡ ከእርሱ ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር።" ይህ እያ... ይህስ አያሳዝነንም ወይ? የሰማይን አምላክ፡ በገዛ

ሐይማኖት ተቋማቸው እና በአዋልዶቻቸው፡ እና በሚያደርጉት ሁሉ ከገዛ ቤተክርስትያኑ አሰወጡት። አሰወጧቸው... እርሱን ከገዛ ቤተ ክርስቲያኑ አሰወጥተው፡ አዋልዶቻቸውን ተቀበሉ።

49 ኢየሱስ በተሰቀለበት ቀን ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ነው። ያውም ነፍሰ ገዳይ የሆነውን፡ በርባንን፡ ተቀብለው ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ነው። ከመካከላቸው “ነፍሰ ገዳይ” መሆኑን የተረጋገጠውን፡ ነፍሰ ገዳይ አሰፈትተው፡ ምን አደረጉ... ሕይወት ሊሰጣቸው የሚችለውን፡ ብቸኛውን ኢየሱስ ክርስቶስን ካዱ።

50 አሁንም የጴንጤቆሰጤ ሐይማኖታዊት ተቋም ጨምሮ፡ እያንዳንዱ የሐይማኖት ተቋም፡ ዛሬም ያሉበት ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። የሐይማኖት ተቋማት ተቋም በሆኑ ለታ እንደሚሞቱ አይተዋል። (በ—በታሪክ ገጾች ውስጥ) ያን ሁሉ ስራዎች ሰርተው ተቋም ከሆኑ በኋላ ወድያውኑ ሳይሞቱ የቀሩ በጭራሽ ታይተው አያውቁም። ተቋም የሆኑ ለታ፡ ምልክቶች ሁሉ፡ ድንቆች፡ ሰጦታዎች፡ እና ሌላው ሁሉ ይተዋቸዋል። ሕይወትን እንዲሰጣቸው ጌታ ኢየሱስን ከመቀበል ይልቅ፡ ወዲያው ተመልሰው በርባንን በመካከላቸው እንዲሆን ፈቱት። አሰከፊ ነገር አይደለም ወይ? እግዚአብሔር ከቤተክርስቲያኑ እንዲወጣ፡ ቆሞ፡ የመጨረሻው የቤተክርስቲያን ዘመን ላይ፡ ለመግባት እንዲሞክር፡ እና እንዲያንኳኳ መደረጉ አያሰደንቅም።

51 አሁን፡ ራዕይ መጽሐፍ በሦስት ክፍሎች የተከፋፈለ ሆኖ እናገኘዋለን። የመጀመሪያው የመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ሲሆን፡ ሰለ ቤተ ክርስቲያኒቱ፡ ሰለ መልእክቱ፡ ሰለ መልእኩ... ሰለ ቤተ ክርስቲያኒቱ መልእክ ይመለከታል። ከዚያ በኋላ... ከዚያ በ 3ኛው ምዕራፍ ላይ ትሰወራለች፡ እሰከ 19ኛው ምዕራፍ ድረሰ ዳግመኛ አትታይም፡ በምዕራፍ 19ኛው ላይ ተመልሣ ትታያለች። በዚህ ጊዜ መካከል፡ እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር ይገናኛል። እንግዲህ፡ ከዛ በኋላ፡ በታላቂቱ የኢየሩሳሌም ከተማ መምጣትና፡ እና በዘመን ፍጻሜ፡ የ—የእሰራኤል ሕዝብ መታተም፡ እና የመሳሰሉት መካከል ይሆናል።

52 አሁን፡ ሰለዚህ ዛሬ ማታ... ወዲያውኑ ከዚህ በኋላ፡ ወደ ፍጥሞ ደሴት እንሄዳለን... ዮሐንስ ምን አየ... ፍጥሞ ከ... ከባህር ዳርቻው በምን ያህል ርቀት ላይ እንደምትገኝ ሰንቶቻችሁ ታሰታውሳላችሁ? ምን ያህል ሩቅ ነበረች? ከባህር ዳርቻ፡ ወደ ሠላሳ ማይል ያህል፡ በትክክል። ፍጥሞ ዙርያዋ ምን ያህል ይሰፋል? ጂኦግራፊያዊ ሁኔታዎችን ታሰታውሳላችሁ? በዙሪያው አሥራ አምሰት ማይል ያህል። እና ለሮማውያን፡ እሰረኞችን የሚያሰፍሩባት እንደ ግዞት ታገለግላቸው ነበር። ዮሐንሰ እዚያ ለምን ተገኘ? ምን ሊያደርግ? የሆነ—የሆነ ነገር ሰርቆ ነውን? አይደለም። ምን አደረገ... ህዝቡን እየረበሸ ሰለነበር... ወይሰ ክፉ ነገር በማድረጉ ወደዚያ ወረወሩትን? አይደለም። ታዲያ ሰለምን በዚያ ነበረ? ሰለ እግዚአብሔር ቃልና ሰለ ምሰክሩ፡ ወንጌልን ለመሰበክ።

53 ለበጎ ካልሆነ በቀር በክርሰትያን ላይ የሚደርሰ አንዳች ነገር አለን? የለም፡ የለም፡ የለም። ታዲያ እግዚአብሔር በደሴቲቱ ላይ ብቻውን እንዲሆን ያመጣው ለምንድነው? ይህንን የራዕይ መጽሐፍ ይሰጠን ዘንድ። እያችሁ፡ እግዚአብሔር በፈለገው ሰዓት ከሰይጣን አይን ቢሆን እንኳ የበግ ጸጉር መሞዘዝ ይችላል። አይችልም ወይ? በቀላሉ ይችላል። በጣም እወደዋለሁ።

ምክንያቱ፡ ብልህ መሆን አይጠበቅብኝማ፡ አያችሁ። አሁን፡ ብልህ ብሆን፡ ማንም እንደ እሱ ብልህ ሊሆን እንደማይችል ስለማውቅ ብልህነቴን በተውኩት ነበር። ስለዚህ—ዝም ብዬ… ምንም ቢኖረኝም፡ ራሴን ለእርሱ አስገዛለሁ አድርግ የሚለኝን ብቻ አደርጋለሁ። ይኸው ነው። አንዳንድ ጊዜ ይሆናል ብዬ ከማስበው መንገድ በጣም ይቃረንብኛል። እሱ ከመራ ግን፡ እርሱ ብልህ እንደሆነ፡ አውቃለሁ። እሱ የሚያደርገውን ያውቃል፡ እኔ አላውቅም። ስለዚህ ራሱ እንዲሰራው እፈቅድለታለሁ፡ አያችሁ፡ ከዚያ በኋላ… ሁሉ ሰላም ይሆናል። አያችሁ? እርሱ እንዲያደርገው እፈቅድለታለሁ። ይኸው ነው፡ ወንድም ነቪሌ። አዎን፡ ጌታዬ፡ ራሱ እንዲያደርግ ፍቀዱለት። አያችሁ? እሱ ራሱ የሚሰራውን የሚያውቅ ነው፡ እኔ አላውቅም። አያችሁ? ስለዚህ ምንም አይነት ጉንጉን አበቦች እና ነገሮች እንዲኖረኝ አልሞክርም። ስለዚህ ራሴን ዝቅ አድርጌ፡ "አባት ሆይ፡ አንተ በምትፈልገኝ ጊዜ ሁሉ፡ እነሆኝ፡" እለዋለሁ። እና እንዲህ ከቀጠላችሁ ነገሮች ሁልጊዜ ትክክል ይሆናሉ።

54 ስለዚህ፡ ዮሐንስ፡ በዮሐንስ ላይ እንዲህ ባይሆን ኖሮ—የራእይ መጽሐፍ አይኖረንም ነበር፡ ዮሐንስ ወደ ደሴቲቱ ባይሄድ ኖሮ ይህ አይሆንም ነበር። እግዚአብሔር የራእይን መጽሐፍ ለእኛ የሰጠበት መንገድ ያ ነበር። ያንን መጽሐፍ ለመጨረስ… የራእይ መጽሐፍ ለመጻፍ፡ ለሦስት አመታት ያህል፡ በዚያ የነበረ፡ ይመስለኛል።

55 ስለዚህ፡ በሦስተኛው ምዕራፍ 22ኛ ቁጥር፡ በግብዣው መጨረሻ ላይ እንተወዋለን። "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ ያለው ይስማ።"

56 አሁን፡ 4ኛው ምዕራፍ እንጀምር፤

> **ከዚያ በኋላም፡ አየሁ፡ እነሆም፡ በሰማይ የተከፈተ ደጅ፤ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ… የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ፤ ወደዚህ ውጣና፡ ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር፡ አሳይሃለሁ አለ።**

57 ጥቅስ በጥቅስ እናየዋለን። እዚህ ጋር በመጽሐፍ መልክ፡ የተጻፉ ቅዱስ ቃላት አሉኝ፡ ምን ያህል ዘልቀን እንደምንገባበት አላውቅም። ጌታ ይምራን። አሁን፡ ተከታተሉ፡ ቃሉ እንዲህ ነው፡-

> ከነዚህ ነገሮች **በኋላ** (ከቤተክርስቲያን ዘመን በኋላ)…

58 ከእነዚህ ሁሉ ነገሮች በኋላም፡ እንግዲህ፡ ይህ የሚዛመደው፡ ይህ ነገር በምድር ላይ የሚሆነው ከቤተክርስቲያን ንጥቀት በኋላ ነው። አያችሁ፡ ከንጥቀት በኋላ ነው። ይህ ማለት እስራኤልን እንደገና ለማንሳት ይሄዳል ማለት ነው። ከቤተክርስቲያን ዘመን በኋላ፣ ከቤተክርስቲያን ዘመናት በኋላ፡ እነዚያ… ቤተክርስቲያን ከሙሽራው ጋር እስክትመለስ እስከ ራዕይ 19ኛው ምዕራፍ ድረስ ዳግመኛ አትታይም። ስለ ስርጉ እግዚአብሔር ይመስገን!

59 እስኪ እናንብበው። እያየናቸው በምናልፋቸው ጊዜ እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት ማንበብ ትፈልጋላችሁ? በጣም ጥሩ። ራዕይ 19 እንክፈት። በጣም ጥሩ፡ ወዳጄ፡ ራዕይ 19። ከራዕይ 19፡ 7ኛው ቁጥር ላይ እንጀምር። ቤተክርስቲያኑ እንደገና የምትገለጥበት በዚህ ጊዜ ነው፡ እስከ 19ኛው ምእራፍ ድረስ እንደገና አትታይም።

## የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ፡ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች፤ ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ፡ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።

60 አቤት፡ እ—እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ስብኬ ግማሹን አልሸፍንም። ተመልከቱ፡ "ሚስቱም ራስዋን አዘጋጅታለች።"

61 ቻርሊ፡ ኔሊ፡ እና ሌሎቻችሁ፡ በዚያ፡ ያወራናቸው ነገሮች፡ ሮድኒ ጋርም፡ በቀደምለት ተነጋግረንበታል። አያችሁ? ኤልሳዕ ያንን ልብስ በኤልያስ ላይ በጣለ ጊዜ... ማለቴ ኤልያስ በኤልሳዕ ላይ በጣለበት ጊዜ፥ እጁን ዘርግቶ እንደገና ከላዩ ወስዶ መለሰውና፡ ዮርዳኖስ እስከተሻገረ ቀን ድረስ በራሱ ላይ ለብሶ ተመላለሰ፡ ወደ ተራራው በወጣ በሠረገላም በተወሰደ ጊዜ፡ እንደገና ጣለለት።

62 ክርስቲያን በመጀመሪያ ሲድን ጊዜ፡ ፊቱ ወደ ክርስቶስ ያዞራል፡ ከዚያ እሱ ራሱ ሊያደርገው የሚገባ ነገር አለው። በመቀጠል፡ ንጽሕና ከሌላቸው ልምዶች ሁሉ፡ እራሱን መቀደስ አለበት፡ "ሽክምን ሁሉ አሰወግዱ፡ እራሷን አዘጋጅታለች። ሙሽራዋ ራሷን አዘጋጅታለች!"

63 ከመቀጠላችን በፊት መናገር ያለብኝ፡ አንድ ትንሽ ታሪክ ያስታውሰኛል። ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ ከብዙ ዓመታት በፊት፡ እዚህ ከበሰተ ምዕራብ ነው፡ አርሞር እና ሰዊፍት ማሸጊያ የተባለ ታላቅ ኩባንያ ነበር። ሰራ ሲሰሩ፡ ወደ አንድ ቦታ ይመጡና ከብቶች እና ግጦሽ ይገዛሉ። እና የገንዘብ ዋጋቸው እጅግ ውድ የሆኑ፡ ትናንሽ የከብት እርባታዎች ይገዛሉ፡ እና እንደዚህ አይነት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሄክታር እርሻዎች፡ ትልልቅና ጥሩ የሄርፎርድ ከብቶችን፡ በየክፍላቸው አሏቸው። የራሳቸው... ከግጦሽ ወደ ሌላው ከብት የሚያመላልሱበት የራሳቸው የባቡር ሀዲድ እና ሌላ ነገሮች ባለቤት ናቸው።

64 እና አርሞር እና ሰዊፍት ትልቅ የከብት እርባታ ነበራቸው፡ እና አንድ ቀን እዛ አንድ ፎርማን ነበራቸው፡ የከብት እርባታው፡ የበላይ ተቆጣጣሪ፡ ነበር፡ አራት ወይም አምስት ሴት ልጆች ነበሩት። እና ከዋናዎቹ ከአርሞር ወንድማማች መካከል አንደኛው... ወይም፡ ወንድማቸው ሳይሆን፡ ልጃቸው፡ የከብት እርባታውን መጎብኘት ፈለገ። እርሱም ገና—ያላገባ፡ ወጣት ነበረ። ስለዚህ ልክ በቦታው እንደደረሰ ልጃገረዶቹ በፊቱ እንደሚሽኮረመሙ—የተረጋገጠ ነው። ስለዚህ ሁሉም እስኪመጣ ድረስ ነገሮቻቸው ስለመምጣቱ እየተዘገጃጁ ነው።

65 እዛም እንደደረሰ፡ ሊገናኙት ስለሆነ፡ እስከነ ቀሚሶቻቸው በላዩ ላይ የፈረሰ ግልቢያ ጨዋታ ላይ እንደሚለበስ ልብስ ለብሰዋል፡ ጸጉራቸው ወርዶ ግንባር ፊት በትክክል ተቆርጧል፡ እና የሁሉም ዳሌ በ44 ልክ ሆኗል፡ ባርኔጣቸው ከጭንቅላታቸው ጀርባ ላይ ወርዷል፡ ታውቃላችሁ። ቁርጥ እንደ ትክክለኛ የምዕራብ ሰዎች መሰሉ፡ ስለዚህ ከሴቶቹ መካከል አንዷ ልታገኘው... ከመካከላቸው አንዷ ይህን ወጣት ልጅ ለማግኘት አሰበውበታል።

66 እና ግን አንዲት አባቷ እና እናቷ ሁለቱም የሞቱባት የ—የአጎታቸው ልጅ ከእነርሱ ጋር ትኖር ነበር። የአጎታቸው ልጅ ነበረች፡ እና እዚያ ላለው ሁሉ እንደ ባርያቸው አይነት ነበረች። ዕቃ ማጠብ የመሳሰሉትን፡ የቆሸሹ ሰራዎች ሁሉ፡ መሰራት ግዴታዋ ነበር። እና ምንም ልብስ አልነበራትም፡ እና ከሌሎች-ሰዎች-የተራረፉትን ልብሶች ትቀበል ነበር እና...

67 እናም ልጁ የሚመጣበት ጊዜ በደረሰ ጊዜ፡ ሁሉም ወደ ጋሪ ፉርጎዎቻቸው ገቡ እና፡ ሊቀበሉት፡ እታች ወዳለው ፌርማታ ሁሉም ወጡ። ጠመንጃቸውን እየተኮሱ፡ ፈረሶቹ እየፋነኑ፡ እና ወዘተረፈ። እና ይዘውት እርባታው ወዳለበት ይዘውት መጡ። ያን ቀን ማታ ላይ ታላቅ ፌስታ ነበራቸው። በዚያም በሳርና በኮርራል አጥር ላይ ወጥተው፡ ሌሊቱን በሙሉ፡ ሁሉም ዘፈኑ—ጨፈሩ። ለሁለት ወይም ለሦስት ቀናት እዚያ ቆዩ።

68 ይህ ምስኪን የአጎት ልጅ... አሁን፡ ይህንን ከአንድ ነገር ጋር አመሳስላለሁ። እነዚህ በልብስ ያጌጡ የአጎታችን ልጆች፡ ባለ ታላላቅ ካቴድራሎች እና ድንቅ አብያተ ክርስቲያኖች፡ እና የቆሸሸ ስም ካለ ለጴንጤቆስጤዎች መስጠት ያለበት ይመስላቸዋል፡ ይህ ስህተት ነው። እነሱም የተሳሳተ ነገር ያደርጋሉ፡ ስለነሱ የሚሰማ ነገር ግን የለም፡ እያችሁ። እነሱ እንደ ክላሲካል አይነት ነገር ናቸው፡ ስለዚህ... ምንም አትሰሙባቸውም። ነገር ግን፡ ብቻ አንድ የጴንጤቆስጤ አገልጋይ አንድ ጊዜ ይሳሳት፡ ወንድሜ፡ ልንገርህ፡ በመላ አገሪቱ በየጋዜጣው ይጎሰምለታል። አዎን፡ ጌታዬ። እስኪ አንድ የጴንጤቆስጤ ወንድም ስለ ሕፃን ይጸልይ፡ እና ህጻኑ ይሙት፡ የአገሪቱ ጋዜጦች በሙሉ ይጨናነቃሉ፡ “መለኮታዊ ፈውስ ወግ አጥባቂነት ነው።”

69 እንዲህ ከሆነ፡ ታዲያ ለምን ዶክተሮች ሳይሳካላቸው የሚቀር ኬዝ ሁሉ በጋዜጣ አይጽፉትም? “ለሴት ዝይ የሚደረግ መረቅ፡ የወንዱ ዝይ መረቅም ያው ነውና።” እያችሁ? ስለዚህ፡ ያንን ቢያደርጉ'ማ፡ የሟቾቹን ጽሑፍ ለመጻፍ ጋዜጣው ላይ ቦታ በጠበባቸው ነበር። እዚህ ወደ መካነ መቃብር ወጥቼ “በመለኮታዊ ፈውስ የሞታችሁ ሁሉ ተነሱ፡” ብላቸው፡ ከዚያም “በህክምና ክትትል ስር ሆናችሁ የሞታችሁ ሁሉ ተነሱ፡” ብላቸው፡ አንድ ሚሊዮን ለአንድ ይበልጧቸዋል። ይህም ትክክለኛ አባባል ነው። አንደኛውን ከነቀፉ፡ ሌላኛውም ይንቀፉ። በትክክል። በአመት ግን በመድሃኒት እና በኦፕራሲዮኖች ሚሊዮኖችን ይገድላሉ፡ እና ስለ እነሱ አንድም ቃል ትንፍሽ ሲባል አልሰማችሁም። እያችሁ?

70 ስለዚህ፡ ይህች ምስኪን ልጃገረድ፡ የምትሰራው ሁሉ እሰቸጋሪ ስራ ነበረ። እና፡ እንዳጋጣሚ፡ ወጣቱ ልጅ... አንድ ምሽት እራት አልቆ እየደነሱ ነበርና፡ እንደምታውቁት፡ እያንዳንዳቸው ልጃገረዶች እራሳቸውን አሰማምረው ቆንጆ አድርገው ነበር። እና ይህች ምስኪን ልጃገረድ፡ አንድ ትንሽ ያረጀ፡ የተቦጫጨቀ ቀሚስ ለብሳ ነበር። እና አንድ ምሽት እራት ካለቀ በኋላ በተዘበራረቀ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጣ፡ እቃዎቹን አጥባ የእቃውን እጣቢ ውሃ ለመጣል በጓሮው በኩል ወጣች። እነሆ... እሷ ወደ ሸቦው አጥር ስታማትር፡ የሸቡ አጥሩን ተደግፎ፡ እሱ ቆሟል። “ሄሎ፡” አላት።

71 በጣም አፈረች፡ ምክንያቱም የበላይ ጠባቂ ልጅ፡ ማለት የከብት እርባታው ባለቤት ልጅ ነውና። የተቦጫጨቀ ልብሰ መልበሷን እንዳያስተውል በማለት፡ ድስቱን ዝቅ አርጋ ያዘችው፤ በባዶ እግሯ፡ ወደ ኋላዋ እያየች፡ **እንዲህ** ወደ ኋላ መመለስ ጀመረች።

72 ወደ እርሰዋም ሄዶ፡ “አትፍሪኝ፡” አላት። “አንድ ነገር ልነግርሽ እፈልጋለሁ፡” አላት። እንዲህ አላት፡ “እኔ እዚህ የመጣሁት ለአንድ አላማ ነው፡ የመጣሁት ሚስት ፍለጋ ነው።” “በየቦታው እየፈለግኩ ነበር፡” አላት። “እውነተኛ ሚስት እንደሆነች ያሰብኳትን ማግኘት እፈልጋለሁና፡ በከተማው

ውስጥ ካሉ ልጃገረዶች ማንኛቸውም ማግባት አልፈለኩም፡" አላት። እንዲህም አላት፡ "እስካሁን ካየኋቸው ሴቶች ሁሉ፡ አንቺን እያስተዋልኩሽ ነበር። የአጎታቸው ልጅ መሆንሽን በአንዳንድ በኩል ደርሼበታለሁ።"

"ልክ ነው፡ ጌታዬ፡" ብላ መለሰች።

73 እንዲህ አላት፡ "አንድ ነገር ልጠይቅሽ እፈልጋለሁ። ታገቢኛለሽ? " ለምን፡ ምን ማለት እንዳለባት አታውቅም። በጣም ተጨናነቀች፡ ሰውየውን ምን ብላ መመለስ እንዳለባት አ—አታውቅም።

74 አቤት፡ ምን ተሰምቷት እንደሚሆን እሰባለሁ። አይደል? እኔ ኃጢአተኛው፡ ከንቱ የማልጠቅም፡ ሰካራም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ለኔ እፈልግሃለሁ፡" አለኝ። እንደ'ኔ አይነቱ ሰው ጋር እንዴት መጣ? እንዴትስ "በገነት ቤት እሰጥሃለሁ፡" አለኝ? እንዴት ብሎ "አድንሃለሁ፡" አለኝ? እንደ እኔ ያለ መጥፎ፡ እንዴት ሊሆን ይችላል? እሱ ግን አደረገው!

75 እሷም መለሰች፡ "ጌታዬ፡ እ—እኔ አልሆንህም—እ—እኔ ለአንተ አልሆንም። እንዳንተ ላለ ሰው ሚስት መሆን አልችልም፡" "አንተ ታላላቅ ነገሮች ለምደሃል። እኔ ድሃ ነኝና፡ አንዳች ነገር አላውቅም፡" አለችው።

እርሱም "ለእኔ ግን ምርጫዬ አንቺ ነሽ፡" አላት።

76 ኢየሱስ እንዲሁ ሲላችሁ ደስ አይላችሁም... ? ክርስትያን ለመባል የማትበቁ መሆናችሁ ታውቃላችሁና። እንደ እናንተ፡ አንዳች ነገር ማድረግ አትችሉም ነበር፡ እርሱ ግን... ሌላ አይደለም... እ—እንዲሁ መረጣችሁ። አያችሁ? እርሱ እናንተን የመረጠበት ምሕረት፡ ከ... ከበጎነቱ ነውና። እናንተ አልመረጣችሁትም፡ እሱ እንደመረጣችሁ፡ ታውቃላችሁና። ትክክል።

እንዲህ አለች፡ "እ—እኔ አልሆንህም... " እንዲህ አለች...

77 "ልብስሽን አትመልከቺ። እኔ ማንነትሽን አያለሁ እንጂ፡ ልብስሽን አላይም።" እሱም አላት፡ "ታገቢኛለሽ ወይ? " እና በመጨረሻም ስምምነቱ ተደረገ። እንዲህም አላት፡ "የዛሬ አንድ አመት፡ እመለሳለሁ። አንቺም ተዘጋጂ። ተመልሼ እመጣለሁና አንቺንም በዚህ ሰፍራ አገባሻለሁና፡ የሰርግ ልብስሽን አዘጋጂ። እና ወደ ቺካጎ፡ ወደ ሰፊው ሜዳ አወጣሻለሁ፡ በዚያም የቤተ መንግስት መኖሪያ ይኖርሻል። ያን ጊዜ፡ ድስት አጠባ፡ እና ሌላው ሁሉ ያበቃል።"

78 እነዚያ እህቶቿ፡ ወይም የአጎቷ ልጆች፡ ይህን በሰሙ ጊዜ፡ እንዲህ አሏት፡ "አንቺ ምስኪን፡ ምንም፡ የማታውቂ ሞኝ! እንዴ፡ ሰውየው እንዲህ ማለቱ እንዳልሆነ ታውቂያለሽ!"

79 ዛሬ የሚሉት ነገርስ በትክክል ይህ አይደለምን? "እንዴት ሊሆን ይችላል፡ የራሳቸውን ስም መፃፍ እንኳ የማይችሉ የወንበር-ሰባሪ ሰዎች፡ እንዴት ትክክለኛዋ ቤተ ክርስቲያን ይሆናሉ? እንደዚህ ያለ ቡድን እንዴት ሊሆን ይችላል? " እውነቱ ግን ያ ነው። ለእርሱ ታጭተን ኃጢአታችንን የሚያስወግድ የኢየሱስ ክርስቶስ የእጮኝነት መሳም በልባችን በተሰማን ጊዜ፡ አለም ግልጽ እንደሆነ ሁሉ፡ ተመልሶ እንደሚመጣ አንዳች ነገር እርግጠኛ ያደርገናል። አንድ ቀን ይመለሣል።

80 ዓመቱን በሙሉ ሠርታ፡ ባሪያ ሆና፡ ትንሽ ሰባ-አምስት-ሳንቲም፡ ቆጠበች፡ ያም—ከሚሰጧት የቀን ደሞዟ ነው። እና የሠርግ ልብሷን ለመግዛት፡ ሁሉንም ነገር ለማዘጋጀት ገንዘቧን እያጠራቀመች ቆየች። ኦህ፡ አሳቧ ሁሉ፡ ራሷን ማዘጋጀት ነበር። (እርሱም... "ራሷም አዘጋጅታለች።") የአጎቷ ልጆች እየሳቁባት እና እየተሳለቁባት፡ እሷ ግን ልብሷን፡ የሰርግ ልብሷን አዘጋጀች።

81 በስተመጨረሻም... የመጨረሻው ቀኑ ደረሰ። እራሷን የሠርግ ልብሷን ለብሳ (አቤት!)፡ ሁሉንም በንጽሕና አዘጋጀች። የአጎቷ ልጆች በዙርያዋ ቀርበው በአጠገቧ እየሰገዱ እንዲህ ይሏት ነበር፡ "እሺ፡ አንቺ ቂላቂል ሞኝ። ስሚ፡ እንደ አንቺ አይነቷ ሴት... አገባለሁ አይልምና፡ እንዲህ ማለቱ እንዳልሆነ ታውቂያለሽ።" እሷ ግን፡ ምንም ይሁን ምን፡ እራሷን አዘጋጀች።

82 ስለዚህ ቀኑም ወደ መምሸት በተቃረበ ጊዜ፡ እነሆ ያሾፉባት እና ይሳለቁባት ጀመሩ። በዚህ ሁሉ በቤቱ በር ላይ፡ እየተጠባበቀች፡ እንዲሁ ጸናች። እሷንም... እሱ ምን አለ፡ "ስንት ሰዓት ላይ እደርሳለሁ አለሽ? "

83 "አልነገረኝም፡" አለች። እንደነገረኝ ግን፡ "እንዲህ አለ... አገባሻለሁ ባለኝ ማታ ላይ... ወይም ይህ የእጮኛነት ቀለበት የሰጠኝ ጊዜ ነበር። ነግሮኛል፡ እንዲህ አለኝ 'የዛሬ አንድ አመት፡' ብሎኛል። ስለዚህ አንድ ሰዓት ይቀረኛል።" አሜን፡ ጠበቀች። "አንድ ሰዓት ቀረኝ፡ ሰላሣ ደቂቃ ቀረኝ፡ አሰር ደቂቃ ቀረኝ።" እነሱም ሳቁባት ተሳለቁባትም፡ ሁሉንም ነገር አሏት።

84 በመጨረሻው፡ ግን፡ በዚያ ወሳኝ ሰዓት፡ አሸዋው ከመንኮራኩሮቹ በታች ሲዞር፡ እና ፈረሶች ሲጋልቡ ሰሙ። እራሷን ያዘጋጀችውን ትንሿን ሙሽሪት ማየት እንዴት ያለ ነገር ነበር፡ ከበሩ ውጭ ዘለለች፡ እና በተነሰነሰው በጽጌሬዳ-አበባ ላይ ቆመች፡ ባል ይሆናት ዘንድ፡ ወደምትወደው ሰው እቅፍ ለመብረር ተዘጋጀች። እንዲህ ዘርግቶ እንዲቀበላት፡ እና አግብቶ ይዟት ይሄድ ዘንድ ነው።

85 ወንድሜ፡ ከእነዚህ ቀናት መካከል፡ "ወንበር-ሰባሪዎች" እያሉ የሚቀልዱ እና የሚናገሩት፡ እና—እና "ጴንጤቆስጤ፡" እና የመሳሰሉት ነገሮች የሚሉት... እየጠበቅን ነው፡ አሁንም ትንሽ ጊዜ አለን። "አይ፡ ድሮም እንዲህ ነበሩ ምንም አልተቀየሩም፡" ይሉናል። አይዟችሁ፡ ትንሽ ቀን ይቀረናል። እነሆ እዚህ ቦታ እመጣለሁ ብሎ ቃል በገባበት ሰፍራ፡ በዚያች ሰዓት ይገኛል። ከእነዚህ ቀናት አንድ ቀን በርረን እንሄዳለን። ብቻ ተዘጋጁ! የሠርግ ልብሳችሁን ያዙ! ክፋትን ሁሉ ከልባችሁ አሰወግዱ። ሌላውን በሙሉ...

86 ይህ ቅዱስ ቃል እንዴት እንደሚነበብ እናዳምጠው፦

> **የበጉ ሰርግ ሰለ ደረሰ፡ ሚስቱም ራሰዋን ሰላዘጋጀች፥ ደሰ ይበለን፡ ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።** (ገባችሁ? )
>
> **ያጌጠና የተጣራ፡ ቀጭን የተልባ እግር ልብሰ እንድትጐናጸፍ ተሰጥቶአታል፤ ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነውና።** (እግዚአብሔር ይመሰገን!)
>
> **እርሱም፡** ወደ **በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው ብለህ፡ ጻፍ** አለኝ። **ደግሞም፡ ይህ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ነው** አለኝ።

87 ስለዚህ እነሆ ከቀናት አንድ ቀን፡ እነሆ በሚቀጥሉ ቀናት፡ ደስ የሚሉ ቀናት አየር ላይ እንገናኛለን። ኧሃ-ሃህ። ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ! እራሳችሁ አዘጋጅታችሁ ጠብቁ! ልባችሁን ከክፉ አሳብ ሁሉ አጽዱ። የቱንም ያህል ቢጨልም የቱንም ያህል ቢሳቅባችሁ ቢቀለድባችሁም "ስህተት ሰርታችኋል፡" ቢሏችሁ፡ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ይኑራችሁ። ቅድስናን ለእግዚአብሔር በመኖርን ቀጥሉ። ቀጥሉበት፡ ሰዓቱ ይደርሳል!

88 ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እንደገና በራዕይ 19 ላይ ትገለጣለች፦

ከእነዚህ ነገሮች **በኋላ**... (የቤተክርስቲያንን ዘመን ካየ በኋላ።)

ከዚህም ነገሮች **በኋላ እየሁ፡ እና፡ እነሆም፡ በሩ**...

89 አሁን፡ አስታውሱ፡ ዮሐንስ ፍጥሞ ላይ ነው። የቤተ ክርስቲያንም ዘመናት ሁሉ አልፎ ካየ በኋላ፦

**... አየሁም፡ እነሆም፡ በሰማይም፡ የተከፈተ በር ነበረ፡...**

90 "በር።" በር ማን ነው? ራእይ 3፡8። በራዕይ፡ 3ኛው ምዕራፍ እና 8ኛው ቁጥር፡ "ሥራህን አውቃለሁ። እነሆ፡ ማንም ሊዘጋው የማይችል በፊትህ የተከፈተ ደጅ ሰጥቼሃለሁ፡ ማንምም ሊከፍትም ሊዘጋም አይችልም።" በር እርሱ ነው! በር! ክርስቶስ በር ነው። በቅዱስ ዮሐንስ 10 ላይ፡ "እኔ የበጎች በረት በር ነኝ፡" ብሏል።

91 በድሮዎቹ ከተሞች፡ እረኛው ከበጎቹ ፊት ሲሮጥ ታዩታላችሁ። ከቆጠራቸው እና ሁሉም መግባታቸው ካረጋገጡ በኋላ፡ እርሱ ራሱ ደግሞ በር ላይ ይተኛል። ተኩላ እርሱን ሳይቀሰቅሰው ሊገባ አይችልም፡ ወይም በጎቹ እርሱን ሳይረጋግጡት መውጣት አይችሉም። አቤት፡ እረኛው በር ላይ ስለተኛ በጎቹ ምን ያህል ደህንነት ይሰማቸዋል።

92 ኖህ፡ በብሉይ ኪዳን፡ በመርከቡ ደጃፍ ቆሞ ነበር። ኦህ፡ ሰሙኝ፡ አንዳች ነገር እናገራለሁና! በሩ ላይ ቆሞ ለሚሳለቁበት ሰዎች ንስሐንና ጽድቅን ሰበከላቸው። እርሱ ገብቶ በቆመባት በዚያች በር፡ በዚያች በር በኩል ካልሆነ ማንም ሰው ሊገባባት አይቻለውም። በመርከቧ ውስጥ ከአንድ በር በቀር ሌላ አልነበረም።

93 አሁንም አንድ መንገድ ብቻ አለ! በጣም ጥሩ፡ ወንድሜ... ? ... ወደ ክርስቶስ አካል የሚያስገባ አንድ መንገድ ብቻ አለ። ወደ ሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የሚወሰድ አንድ በር ብቻ አለ፡ ያ በር ኢየሱስ ነው! "በሩ እኔ ነኝ! ወደ በሩ የሚወስደው መንገድ እኔ ነኝ፡ መንገድ እኔ ነኝ። የበጎች በረት በር እኔ ነኝ።"

94 ለዚህች የቤተክርስቲያን ዘመን "እነሆ በፊትህ የተከፈተ በር አዘጋጅቻለሁ፡" ብሎታል። ያንን ለሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ዘመን አላቸው፡ እነርሱ ግን ቸል ብለውት፡ ድርጅት ሆኑ። "እኔ ግን በፊትህ የተከፈተ በር አዘጋጅቻለሁ።" እና፡ ቅድስናን ከተቀበሉ በኋላ፡ "እነሆ የተከፈተውን በር እሰጣለሁ፡" ይህም መንፈስ ቅዱስ ነው፡ አላቸው። "ሁላችንም በአንድ መንፈስ" (እንዴት? ) "አንድ አካል ለመሆን ተጠመቅን እርሱም ክርስቶስ ነው።" ያንን መልእክት በሜቶዲስት ቤተክርስቲያን ፊት አቀረበላቸው

እነርሱ ግን ቸል አሉ። ለመቀደስ መጥተው መንፈስ ቅዱስን ቸል አሉ። ያንን "የተከፈተው በር።" ትዝ ይላችኋል አይደል?

95 ወደ ክርስቶስ እንዴት ትገባላችሁ? በአንድ መንፈስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እርሱም የክርስቶስ መንፈስ ነው። የገባነው፡ በመጨባበጥ፡ ወይም በመረጫጨት አይደለም፡ በአንድ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግን ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል የአካሉ ተካፋዮችም ሆነናል። ወደዚያች በር ለመድረስ በአንድ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው።

96 ይህ በሰማያት የተቀመጠ በር፡ ያንን በር፡ እነሆ ወደ ላይ በተመለከተ ጊዜ ጌታ ኢየሱስን አየ፡ የሚከተለውን ክፍሉን ብቻ ተመልከቱ። ያንን በር፡ ጌታ ኢየሱስ።

**... አየሁ፡ እነሆም፡ በሰማይ፡ የተከፈተ በር ነበረ፡ እንደ መለከትም ሆኖ... ሲናገረኝ የሰማሁት... ፊተኛው** ድምፅ...

97 አሁን ሁኔታው እየተቀየረ ነው። ዮሐንስ ፍጥሞን ሲመለከት ቆይቷል፡ አሁን ግን ቀና ብሎ አየ። ምን? እዚህ ምድር ላይ የሆነ ነገር ሲሆን አይቷል (እነዚህ የቤተክርስቲያን ዘመናት)፡ በሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት ሁሉ፡ እና ከዚያም በኋላ የቤተክርስቲያንን ዘመናት ካየ በኋላ፡ ከዚያም በኋላ፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ካለፉ በኋላ፡ እነሆ ድምፅ ሰማ። እናም ወደ መንግሥተ ሰማይ አሻቅቦ ተመለከተ እና የተከፈተ በር አየ፡ ፊተኛው ድምፅም እንደ መለከት ድምጽ ይመስላል። በጣም ጥሩ፡ ትዕይንቱ ከፍጥሞ ወደ መንግሥተ ሰማያት ተለወጠ።

98 ድምፁ በሰባት የወርቅ መቅረዞች ውስጥ የተመላለሰው ተመሳሳይ ድምፅ ነበር፡ ተመሳሳይ ድምጽ፡ ድምፁ አልተቀየረም። ይህ ድምጽ፡ ግን፡ መጀመሪያ በተናገረው ጊዜ የት ነበረ? በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን፡ ሰንቶች ታስታውሱታላችሁ? ከኋላውም። "በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርኩ፡" ራዕይ 1—1፡10። ስለዚህ እሱ... "በመንፈስ ነበረ።" ማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ በራዕይ 1፡10 እና 13 ላይ አለ፡ "በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርኩ፡ ከኋላዬም እንደ መለከት ድምፅ ሰማሁ ድምጹም እንደ ብዙ ውሆች ድምጽ ነበረ። ለማየት ዞር ስል፡ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል አንድ ቆሞ አየሁ።"

99 አሁን፡ ያን ሁሉ ምስጢርና ሰባት የወርቅ መቅረዞችን ካሳየው በኋላ (ሰባቱን ከዋክብት፡ በራሱ ላይ ነጭ ጸጉር፡ እና የመሳሰሉትን፡ እግሮቹም እንደ ናስ፡ ዓይኖችም እንደ እሳት፡ ምልክቶች ሁሉ)፡ ከሰማይም ያው ድምፅ (ተከታተሉ።) ሲናገረው ሰማ። ቀና ብሎ ሲመለከት የተከፈተ በር አየ። ኦህ! የተከፈተ የገነት በር! የምትገቡበት እንዴት ነው? በክርስቶስ ኢየሱስ፡ አንድ በሆነው በር፡ አንድ መንገድ፡ ሌላ መንገድ የለም።

100 "በሌላ መንገድ የሚወጣ ሰው፡ ሌባና ዘራፊ ነው።" በምሳሌውም በሠርጉ እራት ላይ ልብስ ሳይለብስ ተቆናጥቶ ወጥትቶ የገባው ሰው፡ ጥፋተኛ ሆኖ ስለተገኘ፡ ታስሮ ወደ ውጭ ጨለማ ተጣለ። ወደ ሠርግ እራት መግቢያ፡ አንድ መንገድ ብቻ ነው። በቅርብ ጊዜ እንደሰበክኩት እምናለሁ። አንድ ሙሽራ... በጥንታዊቷ አገር... አንድ ሰው ሲዳር፡ የጥሪ ወረቀት መስጠት ያለበት ራሱ ነው፡ ልብሶቻቸውን ማሳመር ያለበት ራሱ ነበር። ስለዚህ ይህን ሰው በእራት ማዕድ ተቀምጦ ባገኘው ጊዜ፡ በእራት ተቀምጦ... ምሳሌውን ሰንቶች

ታስታውሳላችሁ? አዋና፡ መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ የሆናችሁ ሁሉ። በእራት ማዕድ ላይ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ አንድ ሰው አገኘ።

101 ምን ይሆናል? ሙሽራው በር ላይ ይቆማል ሰዎች ሁሉ የጥሪ ወረቀታቸውን ይዘው ይቀርባሉ። "በእኔ በቀር ወደ አብ ሊመጣ የሚችል የለም። አብ የሰጠኝ፡ ወይም የገበዛቸው ሁሉ፡ ወደ እኔ ይመጣሉ።" ይመጣሉ፡ የጥሪ ወረቀታቸውን፡ በሙሽራው ፊት ያሰረክባሉ፡ ይህም ሰው ሁሉ አንድ አይነት እንዲመስሉ ነው። የጥንት-ዘመን፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይማኖት፡ መልካም ነገሩ ያ ነው፡ ሰው ሁሉ እንዲመሳሰል ያደርጋልና። ሀብታሞችም ሆኑ ድሆች፡ እሰር ይሁን ነፃ፡ ጥቁር ወይም ነጭ፡ ወንድ ወይም ሴት፡ ሁሉም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናቸው። ሙሽራውም በሩ ላይ ቆሞ ጥሪውን ይቀበላል፡ መጎናጸፊያውን በዚህ በወዳጁ ላይ ያደርጋል፡ በዚህም ምክንያት ሀብታም እና ድሆች ሁሉም ይመሳሰላሉ። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እንዲሁ ነው፡ ታላቅ እና ታናሽ ሰው የለም፡ ሁሉም አንድ ሰው ናቸው፡ ሁሉም በክርስቶስ አንድ ናቸው።

102 አሁን፡ ሙሽራው ተመልሶ በመጣ ጊዜ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ አንድ ሰው ተቀምጦ አገኘ ምን የሆነ ይመስላችኋል? "ወዳጄ ሆይ፡ ወደዚህ እንዴት ገባህ፡" ጠየቀው? እርሱም ዝም አለ፡ ይህ ማለት በበር በኩል ሳይሆን በሌላ መንገድ መግባቱን ያሳያል። በመስኮት ገባ፡ ወይም በጓሮ በር ገባ። የቤተ ክርስቲያን አባል መሆኑን ለማሳየት፡ ወዳጄ ብሎ ይጠራዋል፡ "ወዳጄ ሆይ፡ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? " ከዚያም፡ ኢየሱስ ራሱ፡ እንዲህ አለ። በረኛውንም ጠርቶ፡ "እግሩንና እጁን፡ እሰሩት፡" አለው። ልቅሶ፡ ዋይታ፡ እና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወደ ውጭ ጨለማ ተጣለ። ይህ የክርስቶስ የራሱ ቃል ነው፡ (በትክክል።) "ወደ ውጭ ተጣለ።" ምክንያቱም፡ የሠርግ ልብስ ካልለበሰ፡ ከበሩ በሌላ መንገድ እንደመጣ፡ የታወቀ ነው። በበሩ መጥቶ ቢሆን ኖሮ፡ የሰርግ ልብስ ይቀበል ነበርና።

103 ኦህ፡ ይህን ሰሙት! ታዲያ የሰርግ ልብሱ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከሆነ፡ እኛ በምን መልኩ በሌላ መንገድ እንለውጠዋለን? የመጀመርያው የቤተክርስቲያን ዘመን፡ በክርስቶስ ኢየሱስ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቀው በበሩ መምጣት፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት መቀበል፡ የሰርግ ልብሱን መልበስ ከተገባቸው፡ በሌላ መንገድ በየት በኩል እንመጣለን? በሜቶዲስት፡ በባፕቲስት፡ ወይም በጴንጤቆስጤዎች፡ ወይም በሌላ የኃይማኖት ተቋም ከመጣችሁ፡ ታሰራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ ትጣላላችሁ። መንገድ፡ በር፡ እውነት፡ ሕይወት በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ፡ መምጣት አለባችሁ። አሜን!

104 እሺ፡ ራዕይ 21፡ ወይም፡ ራዕይ 1፡10 እና 13፡ አንድ ዓይነት ድምፅ። እናም እሱን ሲያናግረው የሰማው፡ እንደ ንፁህ የመለከት ድምጽ መሆኑን ልብ በሉልኝ። መለከት እንዴት እንደሚጮህ ታውቃላችሁና፡ ሻካራ ድምጽ ነው። መለከት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን ማለት ነው? ጦርነት ነው። በጦርነት ወቅት፡ በማንኛውም ጊዜ መለከት ሲነፋ ትሰማላችሁ... በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን፡ ይህ ከተሰማ ጦርነት ነው፡ ወይም ሊፈጸም የተዘጋጀ መገለጥ አለ ማለት ነው።

105 አሁን፡ እሱ... የቤተ ክርስቲያን ዘመናት፡እና ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶ ካለቀ

በኋላ፡ 4ኛውን ምዕራፍ ለመጀመር በተዘጋጀ ጊዜ፡ የቤተክርስቲያን ዘመን አለቀ። ምድርን ለቆ ሄዷል፡ አያችሁ። አስታውሱ፡ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል፡ ያንን ድምጽ፡ ከበስተጀርባው በተናገረው ጊዜ፡ ስራው አልቋል። አሁንም ያ ድምጽ በሰማይ ውስጥ እየተናገረ ይገኛል። ስለምድነው? ሕዝቡን ስለተቤዠ ነው። ምድራዊ ሥራው ፈጸመ፡ በክብርም ሆኖ፡ ዮሐንስን "ወደዚህ ና!" በማለት ይጠራዋል፡ ኧሃ-ሃህ። አሜን! ይህ በአዲሱ ዓመት ዋዜማ ላይ ጩኸ ጩኸ ያሰብለኛል። ኦህ፡ ማይ! ይኸው ነው። አያችሁ፡ ተዘጋጅ፡ "ወደዚህ ና!"

106 ጦርነት! እነዚያ የእግዚአብሔርን መልእክት ላልተቀበሉ፡ የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኛ የሆነውን፡ መንፈስ ቅዱስን ላልተቀበሉ ሰዎች፡ ይህ የጦርነት ዝግጅት ነው። አሁን በምድር ላይ መቅሰፍቶችን ሊያፈስስ በተዘጋጀ ጊዜ፡ ይህን የጸጋውን መልእክት ለሚቃወሙ፡ ከተዘጋጀላቸው ፍርድ በቀር ሌላ ምንም አይቀርላቸውም። "ወደዚህ ውጣና ከዚህ ቀጥሎ የሚሆነውን ነገር አሳይሃለሁ። ክርስቶስን-በናቁ፡ አምላክ በሌላቸው ኃጢአተኞች፡ ቁጣዬን በእነርሱ ላይ አፈስሳለሁ።"

107 ዝግጅቱን ተመልከቱ። ኦህ፡ እያመሸን በሄድን ቁጥር መረዳት እየጨመራችሁ እና እየጨመራችሁ ትቀጥላላችሁ። ከቦታ ወደ ሌላ ቦታ መጥቀስ አለብን እንጂ፡ ሁሉንም ነገር እዚህ ማግኘት አንችልም። የመጨረሻው መለከት ሲነፋ እና የመጨረሻው ጦርነት ሲደረግ፡ የመጨረሻው ስብከት ሲሰበክ፡ የመጨረሻው መዝሙር ሲዘመር፡ እና በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ላይ ሰንቆም፡ ለእነዚያ እንዴት አስከፊ ነገር ይሆንባቸዋል፡ "ለምን አልተቀበልከውም? የሰጠሁህን ህይወት ምን አደረግክበት?" ተብለህ ትጠየቃለህ፡ ምክንያት ሰጥ ትባላለህ። ከዚያስ?

108 ያን መዝሙር ሰዘምረው ሰምታችሁኛል፡ ወይም ሞክሩት፦

> ከዚያስ? ከዚያስ?
> ታላቁ መጽሐፍ ሲከፈት፡ ከዚያስ?
> መልእክቱን የካዱ ሰዎች
> ምክንያት ሰጡ በተባሉ ጊዜስ—ከዚያስ?

109 ይህ መፅሃፍ የተጻፈ እንደሆነ ሁሉ፡ በዚያ መቆማቸው የማይቀር ነው። እነሆ… በዚያ ትቆማላችሁ ምክንያት ሰጡ ትባላላችሁ። ኦህ፡ እህት፡ ወንድሞቼ ሆይ፡ እነሆ ይከፍለናል፡ ያርመናል፡ እንደ እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች፡ በቀን በየሰዓቱ ራሳችንን እንድንፈትሽ ነው። ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ "ዘወትር እሞታለሁ። እኔ ግን የምኖረው፡ እኔ ሳልሆን፡ ክርስቶስ በእኔ ይኖራል።" አያችሁ? በልዑል ፊት በምን ሰዓት እንደምትጠሩ አታውቁምና፡ እራሳችሁን ፈትሹ።

110 አሁን፡ "የመለከት ድምፅ ሰማ።" በጣም ጥሩ። አስተውሉ፡ እዚህ ላይ፡ በ 1ኛው ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል ላይ፡ ዮሐንስ የተናገረውን አስተውሉ፦

> … **ፊተኛው ድምጽ… ነበር…** እንደ **መለከት ከእኔ ጋር** የተናገረኝ፡ **ወደዚህ ውጣ፡ አለኝ፡…**

ወደዚህ ውጣ! በምድር ሰላለችው የቤተ ክርስቲያንን ዘመናትን አሳይሃለሁ፥ **እሁን** ወደዚህ ውጣ፡ እዚህ የሚፈጸም ነገር አሳይሃለሁ።

111 እነሆ፡ ክርስቶስ ምድርን ትቶ፡ ወደ ክብር ወጥቶ ነበር፡ የቤተክርስቲያን ዘመን አልቋል፡ መንፈሱ እዚህ ጋር እንዳበቃ አሳይቷል። ወደ ክብርም ወጥቶ ዮሐንስን ወደዚያ እንዲወጣ ጠራው፡ ሌላም የሚፈጸም ነገር አሳየው። "ወደዚህ ና ውጣ።"

112 አሁን፡ 2ኛው ምዕራፍ… 2ኛው ቁጥር ላይ፡ ዮሐንስን እናስተውላለን። ልብ በሉ፡ እክሎም ዮሐንስ፡ በፍጥነት፦

**ወዲያውኑም**… (አሜን!)

113 አቤት፡ አሰቂኝ ከሆንኩባችሁ፡ ደስ ሰላለኝ ነው። ዮሐንስ እክሎ፦

**… ወዲያው በመንፈስ ነበርኩ፡…**

114 የእግዚአብሔር ድምፅ ሲናገራችሁ ስትሰሙ፡ የሆነ ነገር ትሆናላችሁ። አሜን! ኦህ፡ በእናንተ ዘንድስ እንዲሁ ነውን? ያኔ በእኔ ላይ በሆነ ጊዜ፡ ከሠላሳ-አንድ ዓመት በፊት ነበር፡ እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያው ሆኜ አላውቅም። እነሆ፡ "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፡ ወደ እኔ ኑ፡ አሳርፋችኋለሁ።" ባለ ጊዜ፡ ለውጦኛል።

115 ዮሐንስ እንዲህ አለ፦

**… ወዲያው በመንፈስ ነበርኩ፡**… (የምን መንፈስ? መንፈስ ቅዱስ። ኦህ!)… **ወዲያው በመንፈስ ነበርሁ፤ እነሆም፡ ዙፋን በሰማይ ቆሞአል፡** በ**ዙፋኑም ላይ፡ ተቀማጭ ነበረ፡፡**

116 እነሆ፡ ዮሐንስ አሁን ምድርን ትቶ ሄዶ ነበር። ክርስቶስ (በመንፈስ ቅዱስ መልክ) ምድርን ትቶ ሄደ እና እንደገና ወደ አካል ተመለሰ። ዛሬ አካሉ በዚያ እንደ መሥዋዕት መታሰቢያ ሆኖ፡ ተቀምጧል። በዚህኛው ምዕራፍ በቀጥታ ወደዚያ እናልፋለን። የክርስቶስ መንፈስ ግን በቤተክርስቲያን ውስጥ ለመኖር፡ በእኛ ውስጥ እንዲኖር ተመልሶ መጣ።

117 አሁን፡ የሰራውን ዘመን መጨረሻ ካሳየ በኋላ፡ ወዲያውኑ ወደ መንግሥተ ሰማያት ዐረገና፡ "ከቤተክርስቲያን ዘመናት በኋላ፡ ከዚህ ነገር በኋላ ምን እንደሚሆን አሳያችኋለሁ፡" አለ። እንዲህ አለው፡ "ዮሐንስ ሆይ፡ ታቹን ለቅቄ፡ ወደ ከፍታው ወጥቻለሁና፡ ከአሁን በኋላ ላናግርህ አልችልም። ና እኔ ወዳለሁበት ውጣ!" አሜን! "እነሆ ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ሁሉ አሳይሃለሁ።" ኦህ፡ ማይ! እምም! ኦህ! በራእይ ተይዞ፡ ወደ ክብር ተወሰደ።

118 የእርሱ ተሞክሮም እንደ ጳውሎስ ዓይነት ሳይሆን አይቀርም። ማስታወሻ ለምትጽፉ፡ ሁለተኛው ቆሮንጦስ 12፡2 እስከ 4 ድረስ፡ ሁለተኛው ቆሮንጦስ… 2 እስከ 4። ጳውሎስም አንድ ቀን፡ በ… በራዕይም እንዲሁ፡ ተወስዶ ያውቃልና። ይህን ታውቃላችሁ? ከዚያም ማንም ሊናገረው የማይገባ ነገር አየ፡ አንዳች ሳይተነፍስ፡ ለአስራ አራት አመት ጠብቆ አቆየው። አያችሁ? በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ግን አዳምጡ።

119 ጳውሎስ ያየውን ነገር፡ ለመናገርም ሆነ ለሕዝብ ይፋ እንዳይሆን ተከለከለ። ኦህ፡ ማይ! እኔም ይችለዋል ብዬ አላሰብም። (ምክንያቱም፡ እኔም አንድ ቀን በመጠኑ ገብኻቻለሁና፡ ልጨርሰው አልተቻለኝም ወደፊትም አይቻልም።) አያችሁ፡ ሊናገራቸው የማይገባው ነገሮችን አ—አይቷል። ወደ

ሦስተኛው ገነት የተወሰደ... ቢሆንም፡ ቃላት አጥሮታል ብዬ እገምታለሁ። አያችሁ፡ ሦስተኛው ሰማይ።

120 ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያይ ግን ምንኛ የተለየ ነበር፡ እርሱም... እንዲህ አለው፡ "ያየኸውን በመጽሐፍ ጻፍና፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ላክ።" ጳውሎስ እንዳይናገር ተከለከለ፡ ዮሐንስ ግን በዘመናት ሁሉ ውስጥ እንዲመላለስ በመጽሐፍ መልክ እንዲያስቀምጠው ተነገረ። ኦህ፡ ማይ! በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ፡ እነሆ አሁን ተገለጠ። በእርሱ ዘመን አልተገለጠም ነበር፡ እኛ በምንኖርበት በዚህ ዘመን ተገለጠ።

121 ኦህ፡ ዮሐንስ፡ ከቤተክርስቲያን ዘመን በኋላ ወዲያውኑ መወሰዱ፡ የተነጠቀችው የቤተክርስቲያን ምሳሌ መሆኑን፡ ልብ በሉ። የቤተ ክርስቲያን ዘመን ካለፈ በኋላ፡ ከዚህች ከሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን በኋላ፡ መነጠቅ ይመጣል። ቤተክርስቲያንም እንደ ዮሐንስ፡ ወደ እግዚአብሔር መገኘት ትወሰዳለች። ኦህ፡ ማይ! ዋው! ይህ ነገር ነፍሴን ያነቃቃታል። በቤተክርስቲያን መነጠቅ ላይ፡ ተወሰደ! እንዲህም አለ... ይህ ቦታ፡ የራዕይ መጽሐፍ፡ የተጻፈው፡ ተመልከቱ፡ በቤተ ክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ላይ ነው።

122 አሁን፡ እዚህ ጋር ለብዙ ዘመናት በብዙ ክርስትያኖች ዘንድ ባረጀ መሰቀያ ተንጠልጥላ የኖረች አሁን ግልጽ ማድረግ የምፈልጋት ትንሽ ነገር አለችኝ። እና ዛሬ ሳጠና፡ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሰጽፍ፡ እና ሰሞችን እና የተለያዩ ቀለሞችን፡ እና ነገሮችን እያፈላልግኩ አሰብ ነበር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደ እነርሱ እንገባለን፡ ቀሰተ ደመና፡ እና ምልክቶች፡ ወዘተ ናቸው። ወደኋላ መለሰ ብዬ እንድመለከታቸው እና ማጣቀስ እንድችል እነዚህን ቅዱሳት መጻህፍት እየጻፍኩ ነበር፡ ምናልባት... ብቀጥል። ምክንያቱም፡ ብዙውን ጊዜ፡ እንደዚህ ባለ ነገር ላይ ልናገር ከሆነ፡ የ... የተለየ ሰለሚሆን፡ በልቤ ለማወቅ እሞክራለሁ። በዚህ መንገድ፡ ትንሽ ጊዜ ሲኖራችሁ ግን፡ ማጣቀስ እወዳለሁ ምክንያቱም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ወደ ኋላ እና ወደ ፊት፡ የሚመላለስ ነውና።

123 አሁን፡ በማቴዎስ 16፡13 ላይ፡ ይህን እናገኛለን፡ ምናልባት ቅዱስ ቃላት ማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ። ምናልባት መመለስ ከፈለጋችሁ... ማቴዎስን... መክፈት ከፈለጋችሁ፡ እንግዲህ፡ ማቴዎስ 16፡13 ላይ ይገኛል። ይኸው... ኦህ፡ ወደኋላ መለሰ ብለን እናነበዋለን፡ ከዚያ በኋላ በትክክል እንይዘዋለን። የማቴዎስ ወንጌል 16ኛው ምዕራፍ፡ ከ 13ኛው ቁጥር። 16፡13 ሰናነብ በጥሞና አዳምጡ፡ "ጴጥሮስ ሲመጣ... " ወይም፡-

**ኢየሱስም** ወደ **ፊልጶስ ቂሣርያ አገር ዳርቻ በደረሰ ጊዜ፡ ደቀ መዛሙርቱን፡ ሰዎች የሰውን ልጅ...** ማን **እንደ ሆነ ይሉታል፡ ብሎ ጠየቀ?**

**እነርሱም፡ አንዳንዱ.... መጥምቁ ዮሐንስ፡ ሌሎችም፡ ኤልያስ፤ ሌሎችም፡ ኤርምያስ፡** ወይም፡ **ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት።**

**እርሱም** አላቸው፡ **እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?**

**ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡ አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።**

**ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡ የዮና-ልጅ ስምዖን ሆይ፡ አንተ ብጹዕ ነህ፦ ... በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ፡ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠል**ህምና **ብፁዕ ነህ።**

**እኔም እልሃለሁ... አንተ ጴጥሮስ ነህ፡ በዚችም ዓለት ላይ፡ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።**

አሁን**ም... የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፥ በምድር የምታሰረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ** ይሆናል፡... **በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ** ይሆናል።

**ያን ጊዜም እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለማንም እንዳይነግሩ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው።**

124 አሁን በደንብ ተከታተሉ። በጣም ጥሩ። “ለጊዜውም... ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እርሱ... ” ሌላም መክፈት እፈልጋለሁ፡ ቀጥላችሁ ማንበብ ትችላላችሁ፡ እዚሁ 28ኛውን ቁጥር ክፈቱት፡ ሌላው ወደየቤታችሁ ሄዳችሁ ታነቡታላችሁና።

**እውነት—እውነት እላችኋለሁ፡ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ፡ እስኪያዩ ድረስ፡** እዚህ **ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ።**

125 ኦህ፡ አሰቡት እስቲ! “እዚህ ከቆሙት አንዳንዶች፡ እዚህ ከቆሙት **አንዳንዶች**፡ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ ሞትን አይቀምሱም።” እንዴት ያለ ንግግር ነው! አያችሁ፡ ሃያሲያኖች ከዚያ በመነሳት ምን አይነቱ ሞኝ ነው ለማለት ይዳዳቸዋል። እንዲህ አይነት ነገር መናገር እጅግ ይወዳል፡ መፈጸሙም የማይቀር ነው እነርሱ ግን አያውቁትም። አያችሁ? በጣም ጥሩ።

126 ከጴጥሮስ አለት መልስ በኋላ፡ ይህም መልሱ ደግሞ ሁላችንም እንደምናውቀው... ቤተ ክርስቲያኑንም በዚሁ ዓለት ላይ እንደሚሰራ ነው። የሮማ ካቶሊኮች፡ ጴጥሮስን፡ ትንሽ ድንጋይ መሆኑን መናገር እንደሚሞክሩት አይደለም። ጴጥሮስ ስለ መገለጡ የሰጠው መልስ ግን፡ ቤተክርስቲያን ማለት ያ ነው። ይህ ሰው የመለሰው መልስ አይደለም፡ ምክንያቱም በኋላ እሱ ራሱ ወደ ኋላ ክዷልና፡ እግዚአብሔር ወደፊት ይገልጠዋል። ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ የሰጠው መልስም አይደለም፡ ምክንያቱ ጴጥሮስ ተናገረ እንጂ፡ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ያውቃሉ። ነገሩ ግን እንዲህ ነው፡ ማለት፡ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሰማይ የተገለጠው መገለጥ ነው። እንዲህ አለው፡ “በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ፡ ሥጋና ደም ከቶ አላስተማረህም። በዚችም ዓለት ላይ፡ መልስ በተሰጠበት ዓለት፡ ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁ፡ የገሃንም ደጆችም አያይሏትም... አያሸንፉአትም።”

127 እዚህ ላይ ገና ወደዚህ ሳንደርስ፡ ጊዜአችን እዚህ እንዳልጨረሰን ተስፋ እናደርጋለን። እና ይህ ነገር ወደ ሰዎች ልጆች ምን ያህል እንደሚደርስ ማየት እንፈልጋለን። እንደው ከተከታተልነው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ታሪክ ነው። በጣም ጥሩ። አዎን፡ የዓለቱ መልስ፡ ጴጥሮስ ማን እንደነበረ... ቤተክርስቲያኑን ጴጥሮስ በመለሰው መልስ ላይ ይገነባታል። እንዲህ አለ፡ “እዚህ ከቆሙት

እንዳንዶች—የእግዚአብሔር ልጅ በመንግሰቱ እስኪመጣ እስኪያዩ ድረስ ሞትን አይቀምሱም።"

128 አሁን፡ "እንዳንዶች፡" ማለቱን አስታውሱ። ይህ ማለት ከአንድ በላይ ማለት ነው፡ አይደለም እንዴ? **እንዳንዶች** ማለት፡ "ከአንድ በላይ" ማለት ነው። አሁን ግን ተመልከቱ፡ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ በዚያ ቆመው፡ ሁሉንም እያንዳንዳቸውን እንዲህ ጠየቃቸው፡ "**ስለዚህ** ጉዳይ ምን ታስባላችሁ? **ስለዚያ** ጉዳይስ ምን ይመስላችኋል? " ግን አላቸው፡ "እዚህ ከቆማችሁ አንዳንዶችሁ፡ እዚህ ከቆማችሁ አንዳንዶች፡ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስክታዩ ድረስ ሞትን አትቀምሱም።" ኦህ፡ ማይ! እንዴት ያለ ንግግር ነው! አስቡት፡ ይህ የተነገረ የዛሬ ሁለት ሺ ዓመት ነው።

129 እንዲህ ይሆን... እንዴ... የእግዚአብሔር ቃል የማይሳሳትም አይደል? የተናገረው ቃል ሁሉስ ይፈጸማል?

130 አሁን፡ ከቻላችሁ፡ ቀጣዩ ከ ማቴዎስ 17ኛው ምዕራፍ እንከፍታለን። እነዚያን በወሰዳቸው ጊዜ... ከጥቂት ቀናት በኋላም ጴጥሮስን፡ ያዕቆብንና፡ ዮሐንስን፡ ምስክር ይሆኑ ዘንድ፡ ለብቻቸው፡ ወደ ተራራው፡ ይዞ ወጣ። ጴጥሮስ፡ ያዕቆብ፡ እና ዮሐንስ፤ የእግዚአብሔርም መንግሥት በኃይል ስትመጣ አይተዋል። የእግዚአብሔርን መንግሥት አመጣጥ ሂደቱን ተመልክተዋል። አሜን! ኦህ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሲመጣ ምን አይነት ሊሆን እንደሚችል ሂደቱን ለማየት ተወሰዱ፡ የሺ አመት መንግሰት አመጣጥ ለማየት። ሂደቱን አዩት።

131 ከተወሰነ ጊዜ በፊት... ብዙ አገልጋዮች፡ ከእነርሱ ጋር ኦራል ሮበርትስ ጨምሮ። ሴሲል ቢ. ዲሚል፡ **ቴን ኮማንድመንትስን** በጻፈ ጊዜ፡ እነ ወንድም ሻካሪያንን፡ ወንድም ሮበርትስን፡ እና በመላው አገሪቱ የሚገኙ ብዙ ሰባኪዎች፡ መምጣት የቻሉ ሰባኪያን ሁሉ ጠራ፡ እና ምስሉ ከመለቀቁ በፊት ወደ ስቱዲዮ እንዲገቡ ጋበዛቸው፡ እና ለህዝብ ከመቅረቡ በፊት ሂደቱን አሳያቸው፡ ለአንዲት ቲኬት በሃያ-አምስት ዶላር ያስከፍላቸዋልና። ግን እሱ... ሃሳባቸውን እንዲሰጡበት፡ ቅድመ ሂደቱን በደንብ አሳያቸው ይህም ምናልባት የሚወጣለት ትችት፡ ወይም ልዩ ልዩ ነገሮች ይኖር ይሆን በማለት ነው። በህዝብ ዘንድ ከመታየቱ በፊት ቀድመው አዩት።

132 ኢየሱስም ሲናገር፡ "እዚህ ከቆማችሁ አንዳንዶች" (አሜን!) "የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ስትመጣ እስኪያዩ ድረስ ሞትን አይቀምሱም፡" ወይም፡ "የሰው ልጅ በመንግሰቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ፡" እንደማለት ነው። "የሰው ልጅ በመንግሰቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ!" ከጥቂት ቀናት በኋላ ጴጥሮስን፡ ያዕቆብንና፡ ዮሐንስን ይዞ ወጣ፡ ወደ ረጅም ተራራ ወጣ፡ በዚያም በፊታቸው ተለወጠ። የጸሐይ እንኳ፡ የልብሱን ድምቀት ያህል፡ አታበራም። በምሳሌዎች ውስጥ ስንት ጊዜ ነካክተነው አልፈናል፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንመለከተዋለን!

133 አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወስዳችሁ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ ማያያዝ ትችላላችሁና። አዎን፡ ጌታዬ። ፍሳሽ እስከማይኖረው ድረስ! ሁሉም በእግዚአብሔር ኃይል የተጠቀጠቀ ነው። ዲያቢሎስ ቢፈልግ እንኳ አይችልም። ትክክል ነው። ምስክርነታቸውን በዚያ ወዳደረጉ ቅዱሳን ሰዎች ውስጥ አልፎ

መግባት አይችልም በእግዚአብሔርም መንግሥት ባመኑ፡ ቅዱሳን መጻሕፍት ሁሉ ወሰደው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የለወሱ፡ በደሙ ውስጥ የታጠቡ፡ ዓለም አልፋ ልትገባባቸው አትችልም፡ ዲያብሎስ አልፎ ሊገባ አይችልም። ሞተዋልና፡ ህይወታቸውም በእግዚአብሔር ማሕተም፡ በመንፈስ ቅዱስ በኩል በክርስቶስ ዘንድ ተሰውራለች። ዲያብሎስ እንዴት ያስቸግራቸዋል? እምም! እነሆ አሁን ያሉበት ሁኔታ፡ ይህ ነውና።

134 በዚህ ቦታ ላይ፡ እነሆ፡ መምጣቱን፡ ወይም ሂደቱን እዩ። በመጀመሪያው የታየው፡ ያየው ነገር... ምን ነበር? በመምጣቱ መጀመሪያ ያየው ሙሴን ነበር፡ እርሱም ከሞት የሚነሡትን ቅዱሳንን ይወክላል። ኤልያስም ደግሞ በዚያ ቆሞ ነበር።

135 ኦህ፡ ምን እንደሚፈጠር እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። በመጀመሪያ፡ ሙሴ ነበረ፡ ይህ ማለት እነዚህ የተኙባቸው ሰድስት ዘመናት፡ ሰድስት የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ናቸው። ይህ ብቻ አይደልም፡ የኋለኛው ቀን መልእክተኛም፡ ከተለወጡት ጋር፡ ከተነጠቁት ጋር፡ እስከነ ቡድኑ አብሮ፡ ኤልያስም በዚያ ነበር። አሜን! ይህም እንግዲህ ለመጪው፡ የመምጣቱ የሚጠባበቅ ነበር።

136 ሁሉም ምን አደረጉ... ? ሁሉም ከእርሱ ጋር ተሰበሰቡ። ኦህ፡ ማይ! ምን ነበር? ለጴጥሮስ፡ ለያዕቆብና፡ ለዮሐንስ የገባው ቃል፡ ፍጻሜ ነበር። በትክክል። ምክንያቱ እንደተናገረው፡ "እዚህ ከቆሙ አንዳንዶች የሰውን ልጅ በመንግስቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ ሞትን አይቀምሱም፡" እነሆ ሂደቱንም በዚያ አዩት። ከዚያም ከዚህ በኋላ፡ ከትንሣኤ በኋላ...

137 ሌላ ነገር ላምጣላችሁ፡ በቅዱስ ዮሐንስ 21፡20 ላይ፡ ኢየሱስ ከሞተ፡ ከተቀበረ በኋላ ይህን ነገር ላሳያችሁ። አንዳንድ ተቺዎች ይህን የጀመሩት ገና ከጅምሩ ነበር። እስኪ አሁን በትምህርቱ ውስጥ እያለን፡ ይህን እናጸዳው። በቅዱስ ዮሐንስ 20፡21 ላይ፡ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተገናኝቶ፡ አሳና እንጀራን በእሳት ላይ መግቧቸው ነበር። በዳርቻው ላይ ሲጓዙ፡ እነሆ ዮሐንስ በደረቱ ተለጥፎ ነበር፡ ጴጥሮስም ጥያቄውን ጠየቀ፡ እንዲህ በማለት፡ "የዚህ ሰው ጉዳይ እንዴት ይሆናል? " ኢየሱስ ዮሐንስን ይወድ ነበርና፡ ዮሐንስም የፍቅር ሰው ነበር። እንዲህ አለ፡ "የዚህ ሰው ጉዳይ እንዴት ይሆናል? ሁኔታውስ በምን መልኩ ይሆናል? የወደፊት ዕጣ ፈንታው ምን ይመስላል? "

138 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡ "እኔ እስክመጣ ድረስ ቢቆይ፡ ምን አግዶህ ነው? ምንድነው? "

139 በዚህም ደቀ መዛሙርቱም ተሳሳቱ፡ "ኢየሱስ እኔ እስክመጣ ድረስ—ይ—ይ 'ይህ ሰው በህይወት ይቆያል ብሏል'" አሉ።

140 ኢየሱስ ግን ምንም ስህተት አልሠራም። እዚህ በራዕይ፡ 4ኛው ምዕራፍ ላይ፡ ክርስቶስ ቃሉን ጠብቋልና! ዮሐንስን ወደ መንግሥተ ሰማያት ወሰዶ ነገሩን ሁሉ ሂደቱን ሁሉ አስቀድሞ አሳየው። ክብር! ቅድመ እይታውን—አይቷልና። በምድር ላይ እንደ ኖረ ሆኖ የቤተ ክርስቲያንን ዘመናት ሲፈጸሙ በሙሉ አየ፡ መላው የራዕይን መጽሐፍ፡ እስከ ጌታ ምጽአት ድረስ አየ። ኦህ፡ ማይ!

141 ተሰፋዎቹ ሁሉ ምን ያህል የማይሳሳቱ እንደሆኑ አያችሁ? አሁን፡ እናንተ ተመርጣችኋል... ያዕቆብ ያንን ሲያደርግ፡ ዮሐንስ፡ ወይም ሌሎቹ ሁሉ፡ ጳውሎስ እንኳ ሊያያት፡ ሊናገር፡ በፍጹም አልቻለም።

እርሱ ያለው፡ “እስክመጣ ድረስ ቢቆይ ለአንተ ምን አግዶህ? ”

142 ይህንም ሲሉ፡ ዮሐንስን መርጦ አወጣው ገና ሳይሞት ነገሩን በሙሉ አሳየው፡ በነገሩ ውስጥ በሙላት ኖረ። ምን እንደሚሆን አሳየው! (ወንድም ፓት፡ አይደንቅም ወይ? ) ኦህ፡ እያችሁ፡ ወደ ላይ ወሰደው። እዚህ ጋር፡ በ 4ኛው ምዕራፍ እና በ 2ኛው ቁጥር ላይ፡ አረጋግጦታል። “የነበረ፡ ያለ፡ የሚመጣ ነገር ሁሉ አሳይቶታል።” የቤተ ክርስቲያንን ዘመንን፡ የአይሁድን መምጣት፡ የመቅሠፍት መፍሰስን፡ መነጠቅን፡ ዳግመኛ ምጽአቱ፡ እና የሺው ዓመት መንግስት፡ እና የዳኑ የዘላለም ቤታቸው ሁሉ አሳየው፡ በዚያ ውስጥ እንደሚኖር በመሆን በውስጡ ኖረ፡ ነገሩ ሲፈጸም አየ። እያችሁ? እያችሁ? ብቻ አንስቶ ወሰደውና የ—የ—የከፈተለትን ፊልም አሳይቶታል፡ ነገሩን ሁሉ እንዴት እንደሚሆን ሂደቱን አይቷል። ኦህ፡ ማይ!

143 ተነጠቀ። የገባውን ቃል በ—በራዕይ 4፡2 ላይ ፈጸመ። ከመሞቱ በፊት በመንፈስ ተነጥቆ በዚያ ውስጥ እንደሚኖር በመሆን ነገር ሁሉ አየው። ሂደቱን በሙሉ—አይቷል። እርሱ ያየው፡ በራእይ ያየው ነገር፡ አሁን የሚፈጸም እርሱ ነው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጌታ ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ በምድር ላይ የሆነው ሁሉ ያ ነው። እነሆ ለእሱ በራእይ አሳይቶታል።

144 እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ... ወይም በዚያ ዘመን ይመጣል ብሏል ያላለ አልነበረም። እርሱ ያለው፡ “እኔ እስክመጣ ድረስ፡ (ወይም)፡ ቢቆይ ለአንተ ምን አገባህ? ” ከዚያ በኋላ ወሰደውና የነገሩን ሂደት ገለጸ እንዲሁም ወደፊት የሚሆን ነገር አሳየው። አቤት፡ ይህ እጅግ ደስ ይለኛል። እምም። ኦህ፡ ማይ!

145 አሁን አስተውሉ፡ ምን ማለት እንደነበረ እንመልከተው፡-

> **ወዲያው በመንፈስ ነበርሁ፥ እነሆም፡ ዙፋን በሰማይ ቆሞአል፡** በላዩም፡ በዙፋኑም ላይ፡ **ተቀማጭ ነበረ።**

146 አስቀድሞ የጠራው “ድምጽ” ነበረ። አቤት፡ ያ ድምጽ! አቤት፡ ከዚያ ድምጽ፡ ከዚያ ከኋላው ከነበረው ድምጽ ማምለጥ አይቻለኝም። ከዚያም ዘወር ብሎ ተመለከተና፡ የቤተ ክርስቲያንንም ዘመናት ሁሉ አሳየው፡ ምክንያቱም **በ**ቤተ ክርስቲያን ዘመናት፡ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል ቆሞ ነበርና። ከዚያም የቤተክርስቲያን ዘመናት ካበቃ በኋላ ድምጽ ሰማ፡ ያ ድምፅ ምድርን ትቶ፡ ወደ ላይ ወጥቷልና። ወደ ክብርም በገባ ጊዜ፡ እንዲህ የሚለው ድምጽ ሰማ፡ “ወደዚህ ና! ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ነገር አሳይሃለሁ።” ኦህ፡ ማይ!

147 ያ ድምፅ! እስኪ ስለዚያ ድምጽ ለአፍታ ያህል እንነጋገር፤ ጽፌ የያዝኩት ቅዱስ ቃል አዘጋጅቻለሁ። ወደ አንደኛ ተሰሎንቄ 4 እንሂድ፡ እና ይህ ድምጽ ምን እንደሚል እዚህ ላይ እንስማው። ኦህ፡ ከመነበቡ በፊት... ያለ አንዳች ነገር፡ ምን እንደሚናገር ሁላችንም እናውቀዋለን፡ አይደል’ዴ? ምን እንደሚሆን እናውቃለንና። “የእግዚአብሔር መለከት ይነፋል በክርስቶስም የሞቱ ይነሳሉ።” ልክ ነው? ማስታወሻ ለምትይዙ፡ አንደኛ ተሰሎንቄ 4፡16 እና 17 ላይ፡ “ድምጹ፡” ያ ድምጽ የክርስቶስ ድምጽ ነው። ልክ ነው? የክርስቶስ ድምጽ!

> **የእግዚአብሔር...** መለከት **ከሰማይ** ይሰማልና፡ **በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤**

**... ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን... ጌታን በአየር** ለመቀበል፤ **ከእርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለንና።**

148 ዮሐንስን “ወደዚህ ና፡” በማለት የጠራው ያው ድምፅ፡ ዮሐንስ እንዲመጣ “ወደዚህ ና፡” ያለው ያው ድምጽ፡ አንድ ቀን ቤተክርስቲያንን የሚጠራት ያው ድምጽ ይህ ነው (አሜን!)፡ ቤተክርስቲያንን ይጠራታል።

149 በተጨማሪ፡ ዮሐንስን ወደዚህ ና በማለት የጠራው ያው ድምፅ፡ የሞተውን አልዓዛርን ከመቃብር የጠራው ድምጽ፡ ይኸው የመላእክት አለቃ ያው ድምፅ ነው። ክርስቶስ የመላእክት አለቃ ድምፅ ነው። “የመላእክት አለቃ ድምፅ፡” እያችሁ። ኦህ፡ አልዓዛርን የጠራው ያው ድምጽ፡ ዮሐንስን የጠራው የክርስቶስ መለከት ድምጽ እርሱ ነው። በአልዓዛር መቃብር ላይ፡ በታላቅ ድምፅ እንደተናገረ አስተውላችኋል። (“አልዓዛር፡ ና ውጣ፡” ብቻ አላለም።) “**አልዓዛር፡ ና ውጣ**!” ከሙታን ዘንድ አወጣው።

150 እርሱም፡ “እነሆኝ፡” አለ። ከሞተ ሥጋውም ከበሰበሰ በኋላ፡ ከሙታን ተለይቶ መጣ።

151 ዮሐንስን “ወደዚህ ውጣና፡ ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ነገር አሳይሃለሁ፡” ያለው ያው ድምጽ።

152 በክርስቶስ የሞቱትን ለማስነሣት የሚሰማው ያው ድምጽ ነው፡ “እነሆ መለከት... ” መለከት! መለከት ምንድን ነው? የክርስቶስ ድምፅ ነው፡ ጠርቶ ያሰወጣው ያ ድምጽ ራሱ ነው። እንደ መለከት ያለ ድምጽ እንዲህ ሲለው ሰምቷል፡ “ወደዚህ ውጣ!” ትንሣኤ እንዴት እንደሚሆን ተመልከቱ? በድንገት፡ በዓይን ቅጽበት ይሆናል። በዚያ ጥርት ባለው ድምፅ፡ ቤተክርስቲያንን እንዲህ በማለት፡ ይጠራታል፡ “ከመካከልዋ ውጡ።” በታላቁ የጥሪ ድምጽ። እግዚአብሔር ሆይ፡ ያን ቀን እኔ ደግሞ እንድሰማ እርዳኝ።

153 በተደጋጋሚ እንደተናገርኩት... አውቃለሁ፡ እንደ ሟች ሰው፡ ሮድኒ፡ በፊቴ የተዘጋጀ ትልቅ የጨለማ በር እንዳለ አውቃለሁ፡ ሞት ይባላል። ልቤ በመታ ቁጥር፡ ወደዚያ በር አንድ ምት እቀርባለሁ። በእነዚህ ቀናት አንድ ቀን ወደዚያ እሄዳለሁ። ነገር ግን እንደ ፈሪ፡ እየጮህኩ እና እያለቀስኩ መግባት አልፈልግም። እራሴን በፅድቁ መጎናፀፊያው ገንዤ፡ ወደዚያ መግባት እሻለሁና፡ በትንሣኤው ኃይል እንደማውቀው፡ ይህን አውቄአለሁና፤ ይህም አንድ ቀን እርሱ ሲጠራ፡ ከሙታን መካከል እወጣለሁ፤ ከፍ ከፍ እንድል ሲጠራኝ፡ የእግዚአብሔር መለከት ሲነፋ በክርስቶስም የሞቱት ሲነሡ፡ በህይወት ከቆየሁ፡ እነሆ በቅጽበት አይን፡ በድንገት እለወጣለሁ፡ ጌታን በአየር ለመቀበል፡ ከሌሎቹ ጋር እሄዳለሁ። ያ የመለከት ድምፅ፡ ጥርት ያለ፡ ታላቅ ድምጽ ይሰማል። እምም። ኦህ፡ እንደ መምጣቱ አይነት፡ ተመሳሳይ ይሆናል።

154 የሚያጠራጥር ድምጽ አይሆንም። ዮሐንስ “ወደዚህ ና!” የሚለው ድምጽ በሰማ ጊዜ የሚያጠራጥረው ነገር አልነበረም፡ እርሱም መጣ። አሜን።

155 አልዓዛርም፡ በሙታን መካከል፡ በመቃብር ውስጥ ሆኖ፡ ነፍሱም፡ የአራት ቀን ጉዞ ርቃ፡ የት እንደነበረ እንጃ፡ ማናችንም የምናውቅ አይመስለኝም። የትም ይሁን ግን፡ አንዳች ልዩነት አልፈጠረም። ብቻ የቆዳ ትሎች ሰውነቱን እየበሉት፡ ገምቶ፡ እየሸተተ የነበረውን ሰው ጥሪ አቀረበለት። ያ ጥርት ያለ የመለከት

ድምፅ እንዲህ አለው፡ "አልዓዛር ሆይ፡ ውጣ!" በዚያም ሞቶ፡ በሰብሶ የነበረ ሰው፡ እየተራመደ፡ ራሱን እየነቀነቀ ከመቃብር ወጣ። ወንድሞች ሆይ፡ የሚያጠራጥር የለም፡ አለ'ዴ? ምንም አጠራጣሪ ነገር የለውም!

156 ዛሬም ጥርት ያለው ድምጹ፡ "ኃጢአተኛ ሆይ፡ ንስሐ ግባ፡ የዘላለም ሕይወትን እሰጥሃለሁ፡" እያለ ሲናገር ተመሳሳይ ነገር ነው። እያንዳንዳችሁ፡ ንስሐ ግቡ፡ ለኃጢአቶቻችሁም ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። መጥሪያው ያ ነው። የሚያጠራጥር ነገር የለውም።

157 እውነት ስለመሆኑ እኔም ምስክር ነኝ። ዛሬ በመላው ዓለም፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምስክሮች አሉ፡ ይህ እውነት ለመሆኑ ምስክር ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ቃል ሲመጣ፡ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቃል መለከት ነው። የቃሉ ድምፅ ሁሉ መለከት ነው፡ የወንጌል መለከት ነው። ድምጹ ሲሰማም፡ እውነተኛ ነው። "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ትናንትናም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡" ሲባል፡ አንዳች የሚያጠራጥር ነገር የለበትም። እሱ ያው ነው! አዎን፡ ጌታዬ።

158 "ንስሐ ግቡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ።" አንዳች የሚያጠራጥር ነገር የለበትም።

159 "ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው። በእኔ የሚያምን፡ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ለዘላለም አይሞትም። ይህን ታምኛለሽን?" አንዳች የሚያጠራጥር ነገር የለበትም፡ "በሕይወት ይኖራል!"

160 "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፡ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።" አንዳች የሚያጠራጥር ነገር የለበትም፡ አንዳችም የለም፡ የታመነ ድምጽ ነው።

161 ኦህ፡ እኔም አውቀዋለሁ፡ እኔ፡ ትንሹ ኃጢአተኛው ሰው፡ አንድ ቀን በምስኪኑ አይሪሻዊ ልቤ ሲናገር ሰምቼዋለሁ። ይህ ለእኔ እንዴት ሊሆንልኝ ቻለ? እኔ ግን የታመነ ድምጽ መሆኑን አመንኩት፡ ተቀበልኩት። እውነት ስለመሆኑ እኔም ምስክር ነኝ።

162 አንድ ቀን እንደገና ይጠራል፡ ከአለም ወጥተን እንሄዳለን። **ስለዚያ** መለከት የሚያጠራጥር አንዳች ነገር የለም። አዎን፡ ጌታዬ። ከእንግዲህ፡ የሚያጠራጥር ድምጽ አይኖርም፡ አዎን፡ ጌታዬ።

163 ዛሬ ሲጠራን ይሰማል፡ ምንም ነገር ከሚነግረን ነገር ጋር አንድ አይነት ነው።

164 አሁን፡ ወደ ጥቅሱ እንመለስ፦

**እነሆም፡... ዙፋን በሰማይ ቆሞአል፡ (2ኛ ቁጥር) በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ።**

165 ይ ህን ያዙ፡ "ዙፋን፡" በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ። አሁን በምድር ላይ፡ በመቅረዞች መካከል ለመሆን ወደ ኋላ አልተመለሰም። ንጥቀት ሆኗልና። በክብር ነበር፡ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ነበር። ዝቅ ብላችሁ ይህን እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ፡በምዕራፍ 5 ላይ ሳይቀር ሰንመለከተው፡ የምሕረት ዙፋን አልነበረም። ከእንግዲህ የምሕረት ዙፋን ሳይሆን፡ የፍርድ ዙፋን ነው። ከውስጡ

እሳት እና መብረቅ እና ነጎድጓድ ይወጣልና የፍርድ ዙፋን እንጂ፡ የጸጋ ዙፋን አልነበረም፤ ከእንግዲህ፡ ምሕረት አልቋል፡ የቤተክርስቲያን ዘመን አልቋልና። “እርኩሱ ከእንግዲህ ይርከስ፤ ጻዲቁም ከእንግዲህ ይጽደቅ፤ ቅዱሱም ይቀደስ፡” ከእንግዲህ የምህረት ዙፋን የለምና።

166 ዛሬ ማታ፡ ደሙ በዚያ ዙፋን ላይ ተቀምጧልና ምሕረትን ለሚፈልግ ኃጢአተኛው ሁሉ የምህረት ወንበር ነው። በዚያ ቀን ግን፡ ያኔ የምህረት ወንበር አይሆንም፡ የተቆጣ አምላክ የተቀመጠበት የፍርድ ወንበር ይሆናል እንጂ። “እንግዲህ... ጻድቅ በጭንቅ የሚድን ከሆነ፡ ኃጢአተኛውና እግዚአብሔር የማይፈራ ወዴት ይገለጣል? ” እርሱ በክብሩ ደመና ሲመጣ፡ ተራሮች እንኳን መደበቂያ ሰፍራ ለማግኘት ይሞክራሉ። ታዲያ፡ **እኛ** የት እንገባ ይሆን?

ኦህ፡ ፍጹም ብሩክ ምንጭ፡
ኃጢአቴን ያጠበው፤
ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

167 ኦህ፡ ማይ፡ እንዴት ያለ ትምህርት ነው! የሚያጠራጥር ድምጽ አይኖርም! ዙፋኑም፦

... በዙፋኑ**ም** ላይ **ተቀምጧል**። (ከእንግዲህ እዚህ የለም።)

168 እንግዲህ፡ ያ ሌላ ነገር ነው፡ ቤተክርስቲያን ከታላቁ መከራ በፊት መነጠቋን የሚያሳይ ማረጋገጫ ነው። አያችሁ? እንዴት? እነሆ እርሱ በክብሩ ዙፋን ላይ ነው፡ ቤተ ክርስቲያንም ሄዳለች፡ በኋላም መከራው ይመጣል።

169 በኖህ ዘመን አንዲት የዝናብ ጠብታ ከመውደቋ በፊት፡ ኖኅ በመርከቧ ውስጥ እንደነበረ ሁልጊዜ እላለሁ። እሳቱ ሳይወድቅ ሎጥ ከሰዶም ወጣ። ቤተ ክርስቲያንም አቶሚኮች ከመውደቃቸው በፊት ወደ ክብር ትገባለች። አቶሚኩ ከመውደቁ በፊት ነው፡ ትክክል ነው።

170 እስኪ በሉ፡ “የመጀመሪያውስ? ” በአሕዛብ ላይ እንጂ፡ በክርስቲያኖች ላይ አልነበረም።

171 አሁን፡ ልብ በሉ። አቤት! በምድር ላይ ሰራውን ጨርሶ ቤተክርስቲያኑን ወሰዷል፡ አሁን ግን ፍርዱን ላከ። ዓለም እርሱን ተቃወመችው፡ እርሱም ፍርዱን ላከባቸው። እርሱ እና ቤተክርስቲያኑ ግን ወደ ክብር ገቡ።

172 ዮሐንስ፡ በዚያ በፍጥሞ ደሴት፡ የቤተ ክርስቲያን አብርሆት ገላጭ፡ በክብር ከፍ ከፍ ያለች የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነበረ፡ “ወደዚህ ና!” አሳይሃለሁና...

ምን አልክ፡ “የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነው? ”

173 ይህን ቃል ለሚሰማ ሁሉ፡ ዮሐንስ ምሳሌው ነው። አሜን! ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምሳሌ፡ የቃሉ ምስክር ነው። እርሱ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምስክርም ነበር፡ ከክርስቶስ ጋር ባለው የግል ህብረት፡ መላውን ቤተክርስቲያን የሚወክል ነው፡ ማለት፡ በክርስቶስ ያመነ ወንድ ይሁን ሴት፡ ወጣት ይሁን ልጃገረድ፡ እርሱን በተመሳሳይ መመዘኛ የሚቀበሉ ሁሉ፡ እነሆ አንድ ቀን “ና ወደዚህ ውጣ!” የሚለውን የጥሪ ወረቀት ይደርሳቸዋል፡ ከመከራ በፊት ይነጠቃሉ። አስታውሱ፡ የመከራው ሰዓት ገና አልገባም።

174 ይህ ጊዜ፡ ፍርድ የሚመቻችበት ወቅት ነው። ዮሐንስ አሁን ከቤተክርስቲያን ዘመን በኋላ የሚሆነውን እያየ ነው። አያችሁ? እንዲሁ፡ ነበር።

175 አሁንም፡ በ3ኛው ቁጥር፡ ማለቴ 2ኛው ላይ አስተውሉ፡ "ዙፋን በሰማይ ቆሞአል፡ በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ።" አሁን፡ በምድር የነበረው ያው መንፈስ፡ ከዚያ ተነስቶ ወደ ክብር ሄዶ ነበር፡ እና ይህ በምሕረት የተቀመጠ፡ (ማለት ዛሬ ማታ ከእኛ ጋር ያለው ኢየሱስ ራሱ) ወደ ክብር ሄዶ ዙፋኑ ላይ ተቀምጧል።

> በዙፋኑ **ተቀምጦም የነበረው በመልኩ የኢያሰጲድን እና**... **የሰርዲኖን ዕንቍ ይመስል ነበር፤** በ**መልኩም መረግድን የመሰለ፡ ቀስተ ደመና በዙፋኑ** ዙሪያ **ነበረ።**

176 የሚሰብኩ ሌሎች ወንድሞች ሰላሉ፡ እዚህ ጋር አቆማለሁ።

ምናልባት ይህንን፡ ከዚሁ በማለዳ እመለሰበታለሁ። በምሰሉም፡ "እንደ ኤመራልድ ይመስላል።" ኦህ፡ ማይ! ኦህ!

ብዙዎች አሉ ሰዎች በብዙ ሰፍራ፡
ልቦቻቸው የተቀጣጠለ (ይህ ደስ አይላችሁም? )
... በበዓለ ሃምሳ በወደቀ እሳት፡
ያነጻቸው እና ይቀድሳቸው ዘንድ፤
ኦህ፡ አሁንም በልቤ ውስጥ ይነዳል፡
ክብር ለስሙ ይሁን!
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

177 በጌታ በኢየሱስ የተጠራው ዮሐንስ፡ ተጠራና፡ የሰው ልጅ መምጣት እንደሚያይ በእግዚአብሔር ቃል ተገብቶለታል። ጴጥሮስ፡ ያዕቆብና፡ ዮሐንስም፡ በዚያ የቆሙ ሁሉ፡ ኢየሱስ ሲነግራቸው፡ "እዚህ ከቆሙት አንዳንዶች የሰው ልጅ መምጣት እስኪያዩ ድረስ ሞት አይቀምሱም።" እዚያ የቆሙት **አንዳንዶች** እንጂ፡ **ሁሉ** አላለም። እነርሱም ሄዱ፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ፡ የትንሳኤው ሂደት፡ እና የጌታ አመጣጥ እንዴት እንደሚሆን አዩ።

178 ኤልያሰ የሞቱትን ቅዱሳን ወክሎ... ሙሴን ማለቴ ነው፡ እና ተነሳ። ኤልያሰም የሚነጠቁትን የሚወክል ነው። አስታውሱ፡ በመጀመሪያ ሙሴ ነው፡ ከዚያም ኤልያሰ። ኤልያሰ የመጨረሻው ዘመን መልእክተኛ ነው፡ ከእርሱ ጋር ደግሞ የእርሱ ዘመን ወገኖች በትንሳኤ ይመጣሉ... ይመጣሉ... አዎን፡ ማለቴ፡ ተነጥቀው ይመጣሉ። ሙሴ በትንሳኤ ኤልያሰም በንጥቀት የየዘመናቸው ህዝብ ይዘው ይመጣሉ። እና፡ በዚያም፡ ሁለቱ በዚያ ባህርያት የተወከሉ ነበሩ።

179 ጥቂትም ቆይተው አዩአቸውና፡ አይተውም፡ ጴጥሮሰ እንዲህ አለ፡ "ሶስት ዳሶች እንሥራ። አንዳንዶች ከህግ በታች ይሂዱ፡ አንዳንዶቹም ከኤልያሰ ጋር፡ እኛም ደግሞ (አንዳንዶች) **በዚህ** መንገድ።"

180 እነርሱም ገና ሲናገሩ፡ ድምፅ ተናገረ እንዲህም አለ፡ "የምወደው ልጄ ይህ ነው፡ እርሱን ሰሙት።" ቀና ብለው ሲመለከቱ፡ እነሆ ነገር ሁሉ ወደ አንድ ተጠቀለለና፡ ኢየሱስን ብቻውን አዩት። እነሆ፡ እርሱም ብርሃን፡ እውነት፡ መንገድ፡ በር፡ ቀስተ ደመና እርሱ ራሱ ነበረ።

181 ኦህ፡ ነገ፡ ጌታ ቢፈቅድ ታላቅ ትምህርት እንማራለን። ነገ "ፍርዶችን" እናያቸዋለን፤ "የሰርዲዮንን ዕንቍ" እናያለን፡ ምን እንደሚወክል፡ ምን አይነት ድርሻ እንደሚጫወት እንማራለን። እና እ—እ—እነ "ኢያስጲድን" እና ሌሎች... ሁሉም የተለያዩ ድንጋዮች እናያቸዋለን፡ እነዚህንም ሁሉ በሕዝቅኤል በኩል ወርደን፡ ወደ ኦሪት ዘፍጥረት፡ ወደ ራዕይ እንመለሳለን፡ ከዚያም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መኃል ወርደን፡ እነዚህ ልዩ ልዩ፡ ዕንቆችን እና ቀለሞችን፡ አንድ ላይ እናሰራቸዋለን። እንደገና በቀጥታ ወደዚያ አምጥተን ትክክል ካልሆኑ እናያቸዋለን። እያችሁ? እነዚያ ቀለማት እና ሌሎች ነገሮች፡ አንድ አይነት መሆናቸውን እና አለመሆናቸውን እናያለን። እና ያው መንፈስ ቅዱስ፡ ያው አምላክ፡ ቃል እንደገባው፡ አንድ አይነት ምልክቶችን ድንቆችን፡ እና ሰራዎቹን አንድ መሆኑ!

182 ለጴጥሮስ፡ ለያዕቆብና፡ ለዮሐንስ፡ በዚያም ቆመው ለነበሩት፡ ለደቀ መዛሙርቱ ሁሉ፡ እንዲህ አላቸው፡ "አንዳንዶቻችሁ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስክታዩት ድረስ ሞትን አታዩም።"

183 ለዮሐንስ እንዲህ አለው፡ ጴጥሮስ... እንዲህ አለ፡ "የእሱ ነገር እንዴት ታደርገዋለህ? እሱኛው... ይህ—ይህ ወዳጅህ፡ ዕጣ ፈንታው ምን ይሆናል? "

184 እርሱም አለው፡ "እኔ ስመጣ ቢያየኝ አንተ ምን አግዶህ ነው? " እስኪያይ ድረስም እንዲኖር ፈቀደለት! የተቀሩት ሁሉ በሞት ከተወሰዱ በኋላ፡ ዮሐንስ የጌታ ምጽአት ሂደት እንዴት እንደሚሆን ለማየት ኖረ፡ እሱ ከኖረበት ዘመን ጀምሮ ፍርዱ እስኪያበቃና የሺህ አመት መንግስት እስኪገባ ድረስ ሙሉውን ትዕይንት አይቷል። ዮሐንስ ሁሉንም ነገር አይቷል፡ ሚሊኒየም አልፆ፡ የመንግሥቱ ዘመን ሲጀመር አየ። ስለዚህ ቃሉን ጠበቀ፡ አይደል?

185 በ 2ኛው ቁጥር ላይ ምልክት እናደርጋለን። ጌታ ቢፈቅድ፡ 3ኛውን ቁጥር በማለዳ እንጀምራለን።

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

186 ወንድሜ፡ እና፡ (እህቴ፡) ዛሬ ማታ፡ በዚህ ቤተክርስቲያን ያላችሁ ሁላችሁ፡ አወቃችሁም አላወቃችሁም፡ አንድ ቀን ጥሪ እንደሚደርሳችሁ፡ የምታውቁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? ተዘጋጅታችሁም ይሁን ሳትዘጋጁ፡ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ጥሪ ይደርሳችኋል። እነሆ መለከቱ ይነፋል፡ ያን ጊዜም፡ ምናልባት ስለ እናንተ ለኩነኔ ይነፋ ይሆናል፡ ዳግመኛ በህይወት ወደማትኖሩበት ምናልባትም በሚሊዮን አመታት ውስጥ በዲያብሎስ የገሃነም ጉድጓድ ውስጥ ትሰቃያላችሁ፡ አልያም ከከበሩ ቅዱሳን ጋር ወደ ከፍታው ይጠራችሁ ይሆናል።

187 እግዚአብሔር ለጴጥሮስ፡ ለያዕቆብ፡ እና ለዮሐንስ ቃሉን እንደጠበቀው ሁሉ፤ ለተወደደው ለገላጩ ለዮሐንስ፡ ቃሉን እንደጠበቀ ሁሉ፤ በቤተ ክርስቲያን ዘመናት ሁሉ የገባውን ቃል እንደጠበቀ ሁሉ፤ በዚህ በመጨረሻው ቀን የኋለኛው ዝናብ እንደሚያወርድ ቃል መግባቱ የታወቀ ነው እርሱ በምድር በነበረ ጊዜ በእርሱ ዘንድ የነበረው ያው መንፈስ ይልካል፡ ሲመሽ ያን ጊዜ ብርሃን ይሆናልና ያን ኃይሉ፡ እና ምልክቶቹ፡ እና በዘመኑ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ እንደገና ያደርጋል በዚህ በመጨረሻው ዘመን "በተከፈተው በር" እንደገና እንዲሁ ያደርገዋል።

188 ይኸው! አሁን በመካከላችን አለ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ትላንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነው። ለእናንተም... እነሆ እየተሰበከ ነው፡ እየተማራችሁ ነው፡ ስህተትን ከእውነት ማየት እንድትችሉ እየተደረገ ነው። እሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ በሰው ከንፈር እየተናገረ ይገኛል፡ በሰዎች መካከል እየሠራ፡ ምሕረትንና ጸጋን ለማሳየት እየሞከረ ነው።

189 እናንተም እስካሁን ድረስ አልተቀበላችሁትም፡ ስለዚህ በዛሬው ምሽት አዲስ አመት ዋዜማ እጃችሁን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታችሁ፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ በተጠራሁ ጊዜ እርሱ እንዳደረገው በሰላም በፊትህ እቀርብ ዘንድ፡ በዮሐንስ ላይ የነበረውን ኃይል እንድቀበል እርዳኝ" ትላልችሁን? እጃችሁን አንሱ። እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክሽ። መላው ቤተ ክርስቲያን። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። "ጥሪዬን ለመመለስ ዝግጁ ልሁን።"

190 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ በአዲሱ ዓመት ዋዜማ... ከሁለት ሰዓታት በኋላ ያበቃለታልና፡ እነሆም አዲስ ዓመት ይሆናል። በዚህ አመት የሰራነውን ሰርተናል። ጌታ ሆይ፡ እነሆ፡ በሰራኋቸው ብዙ ነገሮች፡ እያፈርኩ፡ ለራሴ ንስሓ እገባለሁ።

191 ብዙዎቹ ወንድሞቼ ያልተረዱት ያደረክኩት ብዙ ነገር ይኖራልና። ብዙዎቹ ወንድሞቼ እኔ በመስክ ላይ ያደረግኳቸው ነገሮች ለምን እንዳደረኩት አያውቁምና። ነገር ግን፡ አባት ሆይ፡ እንዲሁ አደርግ ዘንድ ተመርቼ አደረግኩ። አባት ሆይ፡ በዚ ምሪት እንዳፍር ፈጽመህ አትፍቀድ፡ እጸልያለሁና። ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ እንድሰራው እንደተመራሁ ማድረግ እንድቀጥል ምራኝ። አምላኬ ሆይ፡ እርዳኝ፡ ፈቃድህን አውቄ መፈጸም እችል ዘንድ፡ በቅንነት እሻለሁና (ከብዙ ዓመታት በፊት ከዚህ ቤተ ክርስቲያን ሰወጣ እንዳሳየኸኝ) የሕይወት እንጀራ ለዓለም ሕዝብ አሰይተኸኛልና። ታላቁን የእንጀራ ተራራ ባየሁ ጊዜ፡ ያን ጊዜ ከዚህ ከሕይወት እንጀራ ይበሉ ዘንድ ከምድር ሁሉ ነጭ-ልብስ የለበሱ ሰዎች ሲመጡ አየሁ። አምላክ ሆይ፡ አቤቱ—አምላክ ሆይ፡ ህዝብህን ከህይወት እንጀራ መመገብ በፍጹም፡ በፍጹም እንዳይሳነኝ እለምንሃለሁ።

192 አሁን እጆቻቸውን ያወጡትን እነዚህ የተራቡ ነፍሶችን ባርካቸው። ህይወትን አብዝተው ይናፍቃሉና። ጌታ ሆይ፡ ሁሉንም፡ በመንፈስ ቅዱስ እንድትሞላቸው እጸልያለሁ። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። በረከትን ሰጣቸው። ወንድሞቻችንን፡ በሁሉም ቦታ እርዳቸው።

193 እንደገና ወደዚህ ለመውጣት የሚዘጋጁትን አገልጋይ ወንድሞቻችንን ባርክ፡ ከአፍታ በኋላ፡ ሌሎች ደግሞ ይሰብካሉና። አባት ሆይ፡ ድምጹን ለመሰማት በፍርሃት እና በጥሞና እናዳምጣለንና፡ በዚህ ምሽት የህይወት እንጀራን እንዲሰጡን እንጸልያለን። ይሁን።

194 አቤቱ ባርከን። አዲሱ አመትም በአዲስ ተሰፋዎች ይሞላ፡ አዳዲስ ሀሳቦችን፡ አዲስ መገለጦችን፡ አዲስ ኃይልን፡ ኦህ፡ ሁሉንም ነገር ያምጣልን። ጌታ ሆይ፡ በረከቶችህና፡ ቃል ኪዳኖችህ ዳግመኛ የሚያድሰልን ይሁን። በጸሎታችን፡ ራሳችንን፡ ለአንተ ሰጠን። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም። አሜን።

ወንድሞቼ እና እህቶቼ፡ አመሰግናለሁ።

195 [ወንድም ኔቪል እንዲህ ተናገረ፡ ሁላችንም እንዲሁ በእርጋታ ስለነበርን እንደተባረክንበት አምናለሁ እና ወንድም ብራንሃምን ይህን የምሽቱ መልእክት

ሲያመጣልን መስማታችን ብንቀጥልም እጅግ ደስ ይለን ነበር። እግዚአብሔር በውስጡ እንዳለ ስለምናውቅ የሚያበረታታን መልእክት ነው። አሜን።] ጌታ ይመስገን!

196 [የተናገረውንም ሁሉ እስከ ምጽአቱ ድረስ ሊፈጽመው ቻይ ነውና።] አዎን። [ደግሞም ያደርገዋል፡ ይህ ብቻም አይደለም፡ ብዙ ጊዜ እንደተናገርኩት... ሰዎችን ብዙ ጊዜ እንዲህ እንላቸዋለን፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ሊፈውስህ እንደሚችል ታምናለህ?" እና፡ እርግጥ ነው፡ እንዲያስቡበት ልታደርጓቸው ትችላላችሁ። ይሁን እንጂ ዋናው ነገሩ፡ "**አሁን** እንደሚፈውስህ ታምናለህ ወይ ነው?"] አሜን! [ከዚያም አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡ "እንጃ፡ እኔ አላውቅም።"]

197 [አሁን በሆስፒታል ውስጥ ያረፈች ሴት፡ እሷን ለማየት ገብቼ፡ አልኳት፡ "እህቴ፡ አሁንም ኢየሱስ እንዳዳነሽ ታምኛለሽን?"]

[እሷም አለች፡ "አዎን፡ አምናለሁ።"]

[እኔም አልኳት፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚፈውስ ታምኛለሽ?"]

[እሷም "አዎን፡ ጌታዬ፡ አምናለሁ፡" አለች።]

[እኔም አልኳት፡ "አሁን እንደፈወሰሽ ታምኛለሽ?"]

[እሷም "ይሄን እንጃ አላውቅም፡" አለች።]

["እህቴ ተስፋው ላንቺ ነውና፡ አሁን ማወቅ ትችያለሽ፡" አልኳት።] አሜን! [አሜን። ቃል ገብቷልና።]

198 [አሁን፡ ሌላኛው ወንድሞቻችንን ለመስማት ከመቀጠላችን በፊት። በዙሪያችን ብዙዎች እና ይሄም አሉ... በአዲስ ዓመት ዋዜማ፡ አስቀድሞ የተዘጋጀ-ፕሮግራም የለንም፡ እግዚአብሔር እንዲመራ እና እንዲያሳየን እንዲሁ መጥተን ተሰብስበናል።] አሜን! [እና እንደምታውቁትም፡ ወንድም ፓት ታይለርን ከሰማነው ብዙ ጊዜ ሆኖናል፡ እና ምስክርነቱም ይሁን ወይም ጌታ በልቡ ላይ የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር ይስጠን። ስለዚህ ወንድም ፓት እግዚአብሔር በልቡ ያስቀመጠውን ሁሉ እንዲያመጣ እንጠይቀዋለን።]

199 [ከመምጣቱ በፊት ግን፡ ከኋላ ያለው አንድ ጥሩ ክርስቲያን ወንድም፡ ወንድም ራንዳል ሃይማን፡ በመካከላችን አለ እርሱም ለጌታ እንዲዘምር ጥሩ ጸጋ አለውና፡ ጸጋውን ለእግዚአብሔር ክብር ሊጠቀምበት እንዲችል ፈልጌዋለሁ፡ ስለዚህ ወንድም ራንዳል ወደዚህ መጥቶ እንዲዘምርልን እጋብዘዋለሁ። እዚህ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ዘምሯል እና ፈቃደኛ ከሆነ፡ ችሎታውን ለጌታ ኢየሱስ ዛሬ ማታ እንዲጠቀምበት እጋብዘዋለሁ። አሁን ሊዘምርልን ፈቃደኛ ከሆነ። የሚያግዙት ወጣት ባልደረቦች ከኋላ ተቀምጠዋል፡ ምናልባት ግን እዚህ መጥቶ አሁን እንዲዘምርልን እንጠይቃለን።]

200 [እርሱ ሲዘምር፡ ወንድም ኪንደርን፡ የተወደደ የጴንጤቆስጤ ወንድም በመካከላችን አለ፡ ስለ እርሱም ደስ ብሎናል። እና ወንድም ጄ.ቲ. ፓርነል ምናልባት ከኋላ ሊሆን ይችላል፡ ከውጨኛው ረድፍ በዚህ በኩል የተቀመጠ ይመስለኛል። እና ስለነዚህ ሁሉ መልካም ክርስቲያን ወንድሞች ደስተኞች ነን፡] ቢለርም **በዚያ**። [የእምነት ወንድሞች። እስኪ እንይ፡] ወንድም ቢለር **በዚያ**

ከበስተኋላ አለ። [ወንድም ቢለር፡ እሱም **እዚህ** አለ። አዎን። ወንድም ቢለር እዚህ ነው... —አርታዒ።]

60-1231 ራእይ፡ ምዕራፍ አራት ክፍል 1
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org